



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በዝዋይ ካህናት ማሠልጠኛ የተሠራውን ቤት ለመመረቅ ከቦታው እንደተገኙ ፤

ዋጋው አንድ ብር

# ትንሣኤ



በምድረ ጅቡቲ በመሠራት ላይ የሚገኘው ምሥራቀ ፀሐይ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ይህ ነው ፤

ቁጥር ፹፩

ሰኔ ፲፱፻፷፮ ዓ. ም.

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ። »


አዘጋጅ
ልሣነወርቅ በዛብኅ ፤
ም በሲጠ አበበ



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤


# ማ ው ጫ

## አርእስት ፤ ገጽ


ደብዳቤዎች ..................... ፩
የሰባካ ጉባኤ ሁለተኛ ሥምሪት በአህጉረ ስብከት ..................... ፪
ሁለተኛው አጠቃላይ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ..................... ፬
ዘሪ ሊዘራ ወጣ ..................... ፮
ልማት በቤተ ክርስቲያን ..................... ፰
የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ..................... ፲
አንድ ስኔ የገደለውን ሰባት ስኔ አያነሣውም ..................... ፲፪
ዜና ሊቃውንት ..................... ፲፫
ሁሉም በኀብረት ሳሉ ..................... ፲፭
እንደ አባብ ብልህ እንደ ርግብ የዋህ ..................... ፲፮
ማንን ላግባ ..................... ፲፰
የግብርና በረከት ..................... ፳
ተተኪ ያስፈልጋል ..................... ፳፩
የእርጉዝ ሴቶች የጤና አጠባበቅ ..................... ፳፫
ዓመታዊ በዓሉን አከበረ ..................... ፳፬


# ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት አዘጋጅ
አዲስ አበባ

ሚያዝያ ፲፪ ቀን ፸፯ ዓ.ም. የስቅለት ዕለት የቅዱስ ሚካኤል በዓል ስለሆነ መስገድ አይገባም ከእንገት በላይ ራስን ዘንበል ማድረግ ነው እንጂ እያሉ የብዙ አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች አገዘው ነበር ፡ ምእመናኑ ግን ስግደቱን እንዳልተውት ታውቋል ።

ይህም በፍትሐ ነገሥት በዓለ ወልድ የእመቤታችን ድንግል ማርያም በዓል የቅዱስ ሚካኤል በዓል በሕማማት ሲውሉ አንገትን ዘንበል ማድረግ ነው እንጂ አይሰገድም ተብሎ ተጽፏል ይባላል ።

አትስገድ ብሎ መከልከል ይገባልን? ይህ በየጊዜው የሚደርስ ችግር በመሆኑ ለቅዱስ ሲኖዶስ ቀርቦ የማያዳግም ውሳኔ ቢሰጥበት መልካም ይመስለኛል

አምበሉ ከበደ
አዲስ አበባ

አቶ አምበሉ ከበደ ስለአቀረቡልን ጥያቄ በጣም እናመሰግናለን ጥያቄው በመላው ክርስቲያን ሕዝብ ልቡና የሚጉላላ ስለሆነ መልስ ሊሰጥበት የሚገባ ጥያቄ ነው ትክክለኛውን መልስ ለመስጠትም ስለሚያስፈልግ ብዙ ሊቃውንትን አነጋግረናል የሕግ መጽሐፍንም ተመልክተናል ።

አንዳንድ ሊቃውንት በዕለተ ስቅለት ማንኛውም በዓል ቢውል ከመስገድ አይከለከልም ሲሉ ሌሎች ደግሞ በጌታችንና በእመቤታችን በዓላት አድንኖ በመላእክትና በጻድቃን በዓላት አስተብርኮ ማድረግ ተገቢ መሆኑን ይናገራሉ ።

በፍትሐ ነገሥት ፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ ፲፬ ከገጽ ፩፻፳ ጀምሮ እንደተጻፈው ደግሞ በዕለተ ስቅለት በዓላት ሲውሉ አትስገድ አይልም ነገር ግን ከማንኛውም ጸሎት ጋር ስግደት መስገድ ተገቢ መሆኑን ይገልጽና የማይሰገድባቸውን ዕለታት ሲናገር እሁድ እሁድ በበዓለ ሃ በጌታችን በዓል በእመቤታችን በዓል አይሰገድም ይላል ።

ያም ሆነ ይህ በዕለተ ስቅለት የጌታችን በዓል ወይም የእመቤታችን በዓል እንዲሁም የቅዱስ ሚካኤል በዓል ቢውል አትስገዱ የሚል መረጃ ስለሌለ በዕለተ ስቅለት ለስግደት ለጸሎት ላንኳሕ የተሰበሰ በውን ሕዝበ ክርስቲያን አትስገድ ብሎ መከልከሉ ተገቢ መስሎ አልታየንም ።

ስለዚህ ጠያቂው እንዳሳሰቡት አስፈላጊ ከሆነ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ በኩል የማያዳግም ውሳኔ ቢሰጥበት እኛም አሳባችን ያው ነው ።

# ዓመታዊ በዓሉን..

ከገጽ ፳፬ የዞረ

አንድ ቃል ተናጋሪ በመሆንና ሁሉም በመተባበር ይህንን ስብከተ ወንጌል ለማቋቋም ታላቅ ተሣትፎ አበርክተዋል አሁንም በማበርከት ላይ ይገኛሉ ።

አቶ አዳነ አንድሰው በተለይም ይህን በመሰለ በዓለም ላይ በዘመናችን ዝናን ያስገኘና ለተተኪ ትውልድም ታላቅ ኩራት የሚሆነውን ፡ እንዲሁም የእግዚአብሔር ልጅ የሆነ ሁሉ ከአምላኩ ጋር መገናኛና መጸደቂያ የሆነውን ታላቅ ሕንፃ ከሚሠሩት የሕንፃ ኰሚቴዎች ጋር በመሆን እስከ አሁን ታላቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል ይህን የመሰለ ሕንፃ ም/ ሊቀመንበር ሆነው ቢያሠሩም ቅሉ ቤ/ ክርስቲያን የሚሠራው ለሕዝበ ክርስቲያኑ መጠቀሚያ መሆኑን በማሰብና እስከ አሁን ሕንፃው እንዲሠራ ቢጥሩም "ይህ ሕንፃ እስኪያልቅ ድረስ ብንሠራ ዋንኛው ገጽታ የሕዝበ ክርስቲያኑ መታነፅና የእግዚአብሔርን ቃል መማሩ ነው" በሚል አስተሳስብና እንዲሁም ሕዝቡን ከሕንፃው ጋር አብሮ በቅዱስ ቃሉ በዚሁ ስብከተ ወንጌል ምክንያት ማንኛውም የእግዚአብሔር ተከታይ የሆነ ሁሉ የእግዚአብሔር ቃል እንደ ውሃ የጠማው እንደ እንጀራ የራበውና እንደ ሰማይ የራቀው ፍጡር ሁሉ በዚህ ስብከተ ወንጌል ምክንያት እንዲጠግብና ከአምላኩም ጋር እንዲገናኝ ፡ እንዲሁም የተዋህዶ ክርስትና እምነቱን ለማወቅና ለማሣወቅ ብሎም ለጽድቅ የሚያስብ አዋቂም ሆነ ልጅ ሽማግሌም በጠቅላላው ከልሂቅ እስከ ደቂቅ የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲማር እነሆ ከላይ በተጠቀሰው ቀን ይህን ስብከተ ወንጌል አቋቁመውልናል ።

ከዚህ ላይ ልንዘነጋው የማይገባን የዚህ የስብከተ ወንጌል የሥራ አስኪያጅ ኰሚቴዎች ስብከተ ወንጌልን ከሌሎች ጋር በመተባበር ካቋቋሙ በኋላ ምን አስተዋጽኦ አደረጉ ? ብለን ከሰበካ ጉባኤው ጋር በመተባበር ልዩ መምህራንን ከጠቅላይ ቤተ ክህነት እየጠየቀ ሕዝበ ክርስቲያኑ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲማሩ የሚያደርገው ይሄው የስብከተ ወንጌል ሥራ አስኪያጅ ኰሚቴ ነው ። በዚህ በስብከተ ወንጌል አማካይነት ባሣየው መልካም ተልዕኮ ለስብከተ ወንጌል ተሣታፊዎችም ሆነ ለሕዝብ ተሽጦ ለቤ/ ክርስቲያን ገቢ ይሆን ዘንድ ልዩ መጽሐፍትን ከበጐ አድራጊዎች አግኝቷል ። ይህም የኰሚቴውና የስብከተ ወንጌል ውጤት ነው ።

በዚህም አንፃር ለሰንበት ተማሪዎች አለኝታ እንደመሆኑ መጠን ከተገኘው መጽሐፍ ቅዱስ ለልጆቹ ኰሚቴው በፈቀደው መሰረት ለሚያገለግሉና ጥሩ አርአያ ለሆኑ ልጆች ሽልማት አድርጓል ወደፊትም ይህ የሥራ አመራር ኰሚቴ ለሰንበት ተማሪዎችም ሆነ በስብከተ ወንጌል ለሚሣተፉ ክርስቲያኖች ሁሉ ሽልማት ለማድረግ በመጣር ላይ ይገኛል ። ምክንያቱም እንደ ቤ/ ክርስቲያናችን ስነ ስርዓት መሠረት ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል በሚለው ሐዋርያዊ መርሐ መሠረት ይህ ኰሚቴም መልካም አላማውን አስቧል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ለሰንበት ተማሪዎች ሕዝበ ክርስቲያኑ መንፈሣዊ ትያትር ይመለከቱበትና ወጣቶችም ያሣዩበት ዘንድ እስቴጅ አሠርቶ በየጊዜው

ወደ ገጽ ፯ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

ርዕሰ አንቀጽ

# የሰበካ ጉባኤ ሁለተኛ ሥምሪት በአህጉረ ስብከት

በአሁኑ ጊዜ በቤተ ክርስቲያናችን ከሚሠሩት ዓበይት ተግባራት እጅግ በጣም ከፍተኛውን ክፍል ይዞ የሚገኘው የሰበካ ጉባኤ እንቅስቃሴ ነው ፤ ሰበካ ጉባኤ ለቤተ ክርስቲያናችን ዕድገት ፤ ለካህናት ኑሮ ማሻሻያ ፤ ለሕዝበ ክርስቲያኑ ሃይማኖትና ሥነ ምግባር መማሪያ ፤ ለድኩማን መርጃ ትክክለኛና አመቺ መንገድ የሚከፍት መሆኑ ስለታመነበት ስመ ክርስትና ሀብተ ወልድና ያለው ሰው ሁሉ ለዚሁ መንፈሳዊ ዓላማ ተባብሮ በመሥራት ላይ ይገኛል ።

የሰበካ ጉባኤ ደንብ ከወጣ ከ11 ዓመታት በላይ ቢሆንም አቋሙን አጠንክሮ ሕዝበ ክርስቲያኑን እያስተባበረ መሥራት የጀመረው ግን ከቅርብ ቀን ወዲህ ነው ፤ ባለፈው ዓመት 1975 ዓ.ም. በግንቦት ወር የመጀመሪያው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ ጉባኤ ተመሥርቶ መዋቅሩ ከላይ እስከታች ከተዘረጋ ወዲህ ካህናቱም ሆነ ክርስቲያኑ የሰበካ ጉባኤን ጥቅም በይበልጥ እየተረዱ ለሥራው ተሳትፎ በማድረግ ላይ ይገኛሉ ።

የሰበካ ጉባኤ መምሪያም ለካህናቱና ለሕዝበ ክርስቲያኑ ተፈላጊዎች የሆኑትን መርሐ ግብሮች እያወጣ ከበላይ አካል በማስፈቀድ ምሑራንን ወደ አህጉረ ስብከት በመላክ ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ ወረዳ ፤ ከወረዳ እስከ አውራጃ ከአውራጃ እስከ አህጉረ ስብከት ትምህርታዊ ቅስቀሳ አድርጓል በማድረግም ላይ ነው ።

በዚህ በያዝነው ዓመት ፲፱፻፹፯ ዓ.ም. በታኅሣሥ ወር ልዑካንን ልኮ በአውራጃ ደረጃ መንፈሳዊ ቅስቀሳ ሲያደርግ ፤ እንዲሁም ከመጋቢት ወር ጀምሮ እስከ ሚያዝያ ፴ ቀን ፲፱፻፹፯ ዓ.ም. ምሁራንን ልኮ የቅስቀሳውንና የሥራውን ውጤት እንዲገመግሙ አድርጓል ። በየአህጉረ ስብከቱ የተላኩት ልዑካንም የግምገማውን ውጤት በሪፖርት አጠናቅረው ይዘው ተመልሰው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በተገኙበት አንድ በአንድ በንባብ ተሰምቷል ።

በተነበቡትም ሪፖርቶች የሰበካ ጉባኤ የተጠናከረባቸውንና የተዳከመባቸውን አህጉረ ስብከት ለመገምገም ተችሏል ፤ በሪፖርቶች ላይ እንደተገለጸው የሰበካ ጉባኤ ያልተቋቋሙባቸው አውራጃዎችና ወረዳዎች ሲኖሩ ይኸውም በአስተማሪ እጦት ምክንያት መሆኑ ታውቋል ።

በሪፖርቱም መጨረሻ ሰፋ ያለ ውይይት ተደርጓል ፤ በአስተማሪ እጦት ምክንያት እስከ አሁን የሰበካ ጉባኤ ያላቋቋሙ ለማቋቋም እንዲችሉ ተዘዋዋሪ ሰባኬ ወንጌል እንዲላክላቸው በሚመለከተው ክፍል ተጠንቶ ወደ ቅዱስነታቸው በመቅረብ ከቅዱስነታቸው መመሪያ ትእዛዝ እንዲሰጥበት ሲሉ የስምሪት ሁለተኛ ሪፖርትን ያጠናቀሩት ልዑካን ተወያይተዋል ።

ቅዱስነታቸውም ጥናቱ በሚገባ ተጠናቆ በቀረበ ጊዜ አስፈላጊውን መመሪያ እንደሚሰጡ ተናግረዋል በሌላ በኩል ደግሞ እጅግ በጣም አሳሳቢ ሆኖ የተገኘው የሰንበት ት/ቤት አለመጠናከሩ ነው ፤ ነገ ከነገ ወዲያ ቤተ ክርስቲያንን የሚረከቧት ልጆች ስለሆኑ ልጆችን በሃይማኖትና በጥሩ ሥነ ምግባር ተንከባክቦ ማሳደግ ተገቢ መሆኑ ስለታመነበት ሰበካ ጉባኤው በሚገባ እንዲያስብበት የሁለተኛው ስምሪት ልዑካን አሳስበዋል ።

ከመጋቢት ወር ጀምሮ እስከ ሚያዝያ ፴ ቀን ፹፯ ዓ.ም. በተደረገው ግምገማ ብዙ ነገሮች ተከሥተዋል ፤ የገንዘብ መቀበያ ካርኒዎች በወቅቱ አለመገኘት ፤ የቀሳውስት የንስሐ ልጆቻቸውን በሰበካ ጉባኤ እንዲመዘገቡ አለማድረግ ፤ የሰበካ ጉባኤ ክፍያም ከ፫ብር ወደ ፮ ብር ከፍ በማለት ሁሉ ተደምረው ለሰበካ ጉባኤ እንቅፋቶች መሆናቸው በልዑካኑ ተጠቁመዋል ።

የጐሉትን ችግሮች መጥቀሳችን ነው እንጂ ሌሎችም ችግሮች ሊኖሩ ይችላሉ ፤ ቢሆንም ችግሮች ሁሉ በአንድና በሁለት ጊዜ ሥምሪት ብቻ ሳይሆን እየደጋገሙ ልዑካንን በመላክ እንደሚወገዱ አይጠረጠርም የሰበካ ጉባኤ መምሪያ ልዩ ልዩ ፕሮግራም እያወጣ በየጊዜው ትምህርታዊ ቅስቀሳን የሚያደርጉ ሰባክያንን በየአህጉረ ስብከቱ ከመላክ ባይቦዝንየሰበካ ጉባኤ ዓላማ ከተፈላጊው ግብ እንደሚያደርስእንተማመናለን ።

እስከ አሁንም ቢሆን የሰበካ ጉባኤን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ የተቃረቡ አህጉረ ስብከቶች መኖራቸው አይካድም ።

በአርሲ ሀገረ ስብከት አራት አውራጃዎች ሃያ ሁለት ወረዳዎች ይገኛሉ ፤ በአሰላ ከተማ የሚገኙት ፳ አብያተ ክርስቲያናት እንደወረዳ ሆነው ሲቆጠሩ ወረዳዎቹ ፳፯ ይሆናሉ ፤ በዚሁ ሀ/ስብከት ፪፻ ፺፯ አብያተ ክርስቲያናት ሲኖሩ አንድ ሺህ አንድ መቶ አሥራ ሦስት ቀሳውስት ፩ሺ፩፻፹፭ ዲያቆናት ፯፻፶፩ መዘምራን በድምሩ ፪ሺ፱፻፶፪ ካህናት ይገኛሉ ።

በሀ/ስብከቱ ከአንድ ወረዳ በስተቀር በቀሩት አውራጃዎችና ወረዳዎች የሰበካ ጉባኤ ተቋቁሞ ሥራውን በሚገባ በማከናወን ላይ ይገኛል ፤ ሕዝበ ክርስቲያኑ በሀ/ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ናትናኤል መንፈሳዊ ትምህርት የሰበካ ጉባኤን ዓላማ በሚገባ እየተረዳ የሚፈለግበትን አስተዋጽኦ በመክፈል ላይ መሆኑ ታውቋል ።

በክፍለ ሀገሩ የሚገኙ ቀሳውስት የንስሐ ልጆቻቸው በሰበካ ጉባኤ የተመዘገቡ እንደሆነ ጥቅማቸው የሚቀርባቸው መስሎ ስለታያቸው ለምእመናኑ ምዝገባ እንቅፋት ሆነው መቆየታቸው ሲታወቅ አሁን የሰበካ ጉባኤን አላማና ጥቅም በሚገባ ስለተረዱ የንስሐ ልጆቻቸውን አትመዝግቡ ከማለት ይልቅ በሰበካ ጉባኤ ካል ተመዘገባችሁ የንስሐ አባት አንሆናችሁም ከሚሉበት ደረጃ መድረሳቸውን ተረድተናል ።

በልማትም በኩል አብያተ ክርስቲያናቱ እየጀመሩ ናቸው የአብያተ ክርስቲያናት ሕንፃ እድሳትና ሥራ የሸንኩርትና የሸንኮራ አገዳ ልማት የዛፍ ተከላ ፤ የጊሾና የእርሻ ልማት በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት አካባቢ መጀመሩ ታውቋል ።

ለነባር አስተማሪዎችና ተማሪዎችም በሰበካ ጉባኤ በኩል አስፈላጊው እንክብካቤ እየተደረገ ነው የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሮችም ትምህርታቸውን በአንዳንድ ችግር ምክንያት ለጥቂት ጊዜ አቋርጠው ቢቆዩም ወደፊት የተለመደ መንፈሳዊ ትምህርታቸውን እንደሚቀጥሉ የሚያጠራጥር ምክንያት አይኖርም ።

የአርሲን ሀ/ስብከት ከሁሉ በይበልጥ የሚያስመሰግነው ከምእመናን በሰበካ ጉባኤ ደንብ የተዋጣው ገንዘብ ማዕከላዊነትን ጠብቆ ለመንበረ ፓትርያርክ ድርሻ ፪ሺ፳፪ ብር ገቢ ማድረጉ ነው ።

ሌሎችስ አህጉረ ስብከት? በሰበካ ጉባኤ በኩል ያላቸው ይዞታ እንዴት ይሆን? ሁሉም የአህጉረ ስብከታቸውን ሰበካ ጉባኤ እንቅስቃሴ በጽሑፍ ቢገልጹልን ለአንባብያን ትምህርት ሊሆን ይችላል ብለን እንገምታለን፡

ከዚህ በተረፈ ቤተ ክርስቲያናችን በሰበካ ጉባኤ በኩል የምታደርገው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ሁሉ በሁሉም አቅጣጫ ያማረና የሠመረ እንዲሆን የሁላችንም ምኞት ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

# ሁለተኛው አጠቃላይ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ


ለሁለተና ጊዜ በመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ የተካሄደው ከግንቦት ፲፬ - ፲፰ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ/ም ነበር የዚህ ታላቅ ጉባኤ ሊቀ መንበር ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሲሆኑ ዋና ጸሐፊው ደግሞ ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ናቸው ።

የጉባኤው ተሳታፊዎች የየአህጉረ ስብከት ሊቃነ ጳጳሳት ፣ ሊቃነ ካህናት ፣ የሰበካ ጉባኤ ምእመናን ተወካዮች የሰንበት ት/ቤት ተማሮችና የካህናት ተወካዮች በጠቅላይ ቤተ ክህነት የመምሪያ ሐላፊዎች የአንደኛና የሁለተኛ የሰበካ ጉባኤ ሥምሪት አባላት ወዘተ ናቸው ።

በጉባኤው መጀመሪያ ግንቦት ፲፬ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. በጠቅላይ ቤተ ክህነት ስብከተ ወንጌል አዳራሽ ከጧቱ በ፪ ሰዓት ተኩል የጉባኤው ተሳታፊዎች የተመደበላቸውን ቦታ ይዘው የቅዱስነታቸውን መምጣት ይጠባበቁ ጀመር ፣ ሦስት ሰዓት ሲሆን ቅዱስነታቸው ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ጋር በመሆን ከስብከተ ወንጌል አዳራሽ እንደተገኙ ጸሎተ ወንጌል ተጀምሯል ።

በመጀመሪያ ቀዳሚሃ ለጥበብ ፈሪሃ እግዚአብሔር ምክር ሠናይት ለኩሎ ዘይገብራ ወስብሐቲሁኒ ይነብር ለዓለም በአማርኛ የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው ፣ ለሚያደርጋት ሁሉ ምክር ያማረች ናት የእግዚአብሔር ምስጋናም ለዘለዓለም ጸንቶ ይኖራል የሚለው መዝሙረ ዳዊት ተሰብኮ ከማቴ. ወን .፲. ፩ - ፲፭ ያለውን ብፁዕ አቡነ ኤልሳዕ የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊና የኢሉባቦር ሀ/ ስብከት ሊቀ ጳጳስ አንብበው ሲያበቁ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጉባኤውን በጸሎት ከፍተዋል ።

ወዲያው ቃለ ጉባኤውን የሚከታተሉ ኮሚቴዎች ተመርጠው የተመደበላቸውን ስፍራ እንደያዙ ጉባኤው ሥራውን ቀጥሏል ። በመጀመሪያ ስለ ተፈጸመው የሥራ ክንውንና ለወደፊቱ ሊደረግ ስለሚገባው ሥራ በሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና የአጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ሊቀ መንበር አጠቃላይ መግለጫ ተሰጥቷል ።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጉባኤውን በመምራት ላይ እንዳሉ

ሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው ባደረጉት ገለጻ ቤተ ክርስቲያናችን ለሕብረተሰቡ ያበረከተችውን ሁሉ በጡትላላ ለመጥቀስ ብዙ ጊዜን የሚጠይቅ መሆኑን ጠቁመው በ፲፱፻፳፩ የወጣው ቃለ ዓዋዲ በ፲፱፻፷ እንደገና ተሻሽሎ ታትሟል በ፲፱፻፷፬ ዓ/ም አገር አቀፍ ሴሚናር ተደርጓል እንዲሁም በ፲፱፻፸፭ ዓ.ም. የመጀመሪያው አጠቃላይ መንፈሳዊ ጉባኤ ተመሥርቶ አሁን በያዝነው ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. የምናካሂደው ከፍተኛ ጉባኤ ሁለተኛ ነው ካሉ በኋላ ስለካህናት የጡረታ አበል ስለድርብ በዓላት አከባበር ስለመቃብር ይዞታ ደረት እየደቁ ፊት እየነጩ የማይገባ ልቅሶ ስለማልቀስ በከተማ የሚኖሩ ካህናት በትርፍ ጊዜያቸው ማከናወን ስለሚገባቸው የልማት ተግባር ወዘተ ቀርቧል ።

ስለገንዘብና ንብረት ስለ ቅጾችና ሞዴሎች በሊቀ ካህናት ክፍሌ ገብረ መስቀል በጠቅላይ ቤተ ክህነት የገንዘብና ንብረት መምሪያ ሐላፊና የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባል ሪፖርት ቀርቧል ።

ክርስቲያን የሕፃናት አስተዳደግ ጉባኤ ዋና ጸሐፊ አቶ ፀጋዬ በርሄ ስለድርጅቱ ተግባር በፊልም የተደገፈ አጭር መግለጫ አቅርበዋል ።

ጉባኤው ከግንቦት ፲፬-፲፰ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. ሲወያይባቸው ሰንብቶ አስፈላጊዎች ናቸው ብሎ ባመነባቸው ነጥቦች ላይ ውሳኔ አስተላልፏል ። ውሳኔውም



ሊቀ ማዕምራን አበባው ይግዛው የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪ ያጅ ለታላቁ መንፈሳዊ ጉባኤ መግለጫ ሲሰጡ

ገልጸው ጉባኤው ተወያይቶ ውሳኔ እንደሚያስተላልፍ ያላቸውን ምኞት ገልጸው ሊቀ ማዕምራን ማብራሪያቸውን አጠቃለዋል ።

ከሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው መግለጫ ቀጥሎ ስለሰበካ ጉባኤ የሥራ እርምጃና ውጤት በመልአከ ታቦር ተሾመ ዘርይሁን በጠቅላይ ቤተ ክህነት የውጭ ጉዳይ መምሪያ ኃላፊና የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ም/ ሊቀመንበር ገለጻ ተደረገ ።

ቀጥሎም ስለስብከተ ወንጌልና የሰንበት ትምህርት ተልዕኮ አፈጻጸምና የሥነ ጽሑፍ ስርጭት በአሁኑ ጊዜና ወደፊት በሚል ርእስ በሊቀ ኅሩያን መርሐ ጽድቅ ገ/ ሕይወት የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ሐላፊና የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ አባል ሪፖርት

ቅርሳቅርስን በሚመለከት በአቶ አሰፋ ወሰን መካሻ ስለሰበካ ጉባኤ የልማት እንቅስቃሴ በአቶ ጌታቸው ዘሩ ሲገለጥ ልማትንና ተራድኦን በሚመለከት በብፁዕ አቡነ ገሪማ በምድረ ሱዳን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ ክርስቲያን ሊቀ ጳጳስና የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ሐላፊ አጠቃላይ መግለጫ ተሰጥቷል ።

የብፁዕ አቡነ ገሪማ መግለጫ እንደተሰማ ቢድንኳን ውስጥ የተዘጋጀው የልማት ውጤት በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ተከፍቷል ። በዚያም የእያንዳንዱ አህጉረ ስብከት የልማት እንቅስቃሴ ውጤት ታይቷል ።

ከዚያም በኋላ በቀሩት ዕለታት ከአህጉረ ስብከት ተጠናቅረው የቀረቡ ሪፖርቶች በንባብ ተሰምተዋል ። እንዲሁም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ግንቦት ፲፰ ቀን ፲፱፻፸፯ ዓ.ም. የአዲስ አበባ አድባራትና ገዳማት አለቆች የሰበካ ጉባኤ ም/ ሊቃነ መናብርት በተገኙበት በሊቀ ማእምራን አበባው ይግዛው የጠ/ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ሊቀ መንበር ተነቧል ሊቀ ማእምራን ውሳኔውን በንባብ ካሰሙ በኋላ የመዝጊያ ንግግር አድርገዋል ።

ቀጥሎም በሰበካ ጉባኤ አደረጃጀትና በቤተ ክርስቲያን የልማት እንቅስቃሴ ብልጫ ላሳዩ አህጉረ ስብከት ሽልማት ተደርጉላቸዋል ። ከሽልማቱ በኋላ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ንግግርና ቃለ ቡራኬ የጉባኤው ፍጻሜ ሆኖአል ። በውሳኔው የተላለፉትን መግለጫዎች በሚቀጥለው እትማችን እናቀርባለን ።

የዜናው አቅራቢ ቄስ ልሣነ ወርቅ



www.ethiopianorthodox.org

# ዘሪ ሊዘራ ወጣ

ገበሬዎች ከሚያመርቱት እህል ጥሩ ውን መርጠው ለዘር ካስቀመጡ በኋላ መሬቱን አርሰው አለስልሰው ይቆዩና የዘር ወቅት ደርሶ ዝናም ሲጥል ያስቀ መጡትን ጥሩ ዘር በመዝራት ለመሬት አደራ ይሰጣሉ ። መሬትም አደራዋን ከ ተቀበለች በኋላ ወቅት ጠብቃ በመጀ መሪያ ቡቃያ ቀጥሎም አበባ ፤ ከዚያም እንቡጥና ዛላ በመጨረሻም ጠቃሚ የ

ልጣን ቢሆንም ለእህል ዘር ምቹ የሆነ ውን መሬት አዘጋጅቶ መዝራት ፤ ማረ ም ፤ መኰትኰትና መንከባከብ የገበሬ ው ግዴታ ነው ። ስለሆነም በሀገራችን በየዓመቱ ሰኔና ሐምሌ በመጣ ቁጥር እ ያንዳንዱ ገበሬ ሞፈር ቀምበሩን አንግቦ

ምህርቱም ኃይለ ቃል የሚከተለው ነው "እነሆ ዘሪ ሊዘራ ወጣ እሱም ሲዘራ አንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ ወፎችም መጥተው በሉት ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫ ላይ ወደቀ ጥልቅ መሬትም ስላልነበረው ወዲያው በቀለ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ ሌላውም በእሾህ መ ካከል ወደቀ እሾህም ወጣና አነቀው ። ሌላውም በመልካም መሬት ላይ ወደቀ



በምሳሌም ብዙ ነገራቸው እንዲህም አላቸው እነሆ ዘሪ ሊዘራ ወጣ እርሱም ሲዘራ አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ ፤ ወፎችም መጥተው በሉት ማቴ ም፣ ፲፫ ቁ፣ ፫

ሆነውን ፍሬ ለባለቤቱ ታበረክታለች። ገበሬው የዘራው የእህል ዘር ለፍሬ በ ቅቶ ባየ ጊዜ ደስታው ዕጥፍ ድርብ ይሆ ናል ። ፈጣሪውንም ከልብ እያመሰገነ በድካሙ ውጤት ይጠቀማል ። ለራሱ ብቻ ሳይሆን ጥቅሙ ለመላው ኅብረተ ሰብ ስለሆነ ደስታው የገበሬው ብቻ ሳ ይሆን የጠቅላላው ኅብረተሰብ ነው ።

ምንም እንኳን የመብቀልና የማደጉ እንዲሁም ለፍሬ የመብቃቱ ጉዳይ የሚ ከናወነው በእግዚአብሔር ፈቃድና ሥ

ዘሩን ተሸክሞ ፤ ወደየእርሻው እየሄደ ተ ገቢውን ዘር በተገቢው ቦታ በመዝራት ለራሱ ከዚያም አልፎ ለሀገርና ለወገን ብዙ በረከትን ያተርፋል ።

የግብርና ሥራ በረከትን የሚያስገኝ ና የተቀደሰም በመሆኑ ጌታችን ኢየሱ ስ ክርስቶስ መምህራንን በገበሬዎች ቃለ እግዚአብሔርን በዘር ፡ የሰውን ል ቦና በመሬት መስሎ በመናገር ትምህር ቱን ለማዳመጥ የተሰበሰበውን ሕዝብ በዘሩ ምሳሌ ቃሉን አስተምሮአል የት

አንዱም መቶ አንዱም ስድሳ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ'' ማቴ. ፲፫ ፡ ፫-፱ ።

በዚህ ምሳሌ መሠረት ዘር የተባለው የእግዚአብሔር ቃል ሲሆን በአራት የ መሬት ዓይነት የተመሰለው ደግሞ የም እመናን ልቡና መሆኑን ጌታችን ኢየሱ ስ ክርስቶስ በዚሁ ምዕራፍ ከቁጥር ፲፰-፳፫ ባለው መስመር ተርጉሞታል ።

1ኛ/ በመንገድ ዳር የተዘራን ዘር ወ ዲያውኑ ወፎች እንደሚለቅሙት ሁሉ ሰዎችም የሚሰሙት ቃለ እግዚአብሔ



ር ለሕይወታቸው መመሪያ ሆኗቸው መ ልካም ሥራ እንዳይሠሩ ሰይጣን ስለሚ ፈታተናቸውና ወዲያው እንዲረሱት ስ ለሚያደርጋቸው እንደነዚህ ያሉት ምእ መናን ልቦናቸው በመንገድ ዳር መሬት ተመስሏል ።

2ኛ/ ጥልቅ አፈር በሌለው በጭንጫ መሬት ላይ የወደቀው ዘር ለጊዜው ከበቀ ለ በኋላ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ወዲያው እን ደሚደርቅ አንዳንድ ሰዎችም ቃለ እግ ዚአብሔር ሲነገራቸው በጽሙና ያዳም ጣሉ ፤ ለጊዜውም ተቀብለው ወዲያው የማይረሱት ይመስላሉ ። ፈተና በመጣ ጊዜ ግን ፈጥነው በመውደቅ እግዚአብ ሔርን እስከመካድ ይደርሳሉ እንደነዚ ህ ያሉትም ሰዎች ልቡናቸው በጭንጫ መሬት ተመስሏል ።

3ኛ/ ደግሞ በእሾህ የታነቀው ዘር ነው ። በእሾህና በአረም የታነቀ ዘር ለ ፍሬ እንደማይደርስ ሁሉ የእግዚአብሔ ርን ቃል ሰምቶ በእምነት የማይፈጸመ ው ነው ።

4ኛው ግን በመልካም መሬት ላይ የ ወደቀው ዘር ምሳሌ ነው ። ጥልቅ አፈር ባለውና በለሰለሰ መሬት ላይ የተዘራ ዘር ገበሬው በመከር ጊዜ ሊያገኝ የተመኘ ውን ተገቢ ፍሬ ሊያፈራ እንደሚችል ን ጹሕ አእምሮና ቀና ልቡና ያለው ምእ መንም በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደ

ደ መሆኑን የሚያመለክት ነው ። በአጠ ቃላይ የምሳሌዎቹን ፍሬ ሃሳብ ስንመ ለከት መልካም ፍሬ ከጭንጫው ወይ ም በመንገድ ዳር ካለውና ከእሾሀማው መሬት ላይ ከወደቀው ዘር ሳይሆን ጥል ቅ አፈር ካለው መልካም መሬት ላይ ከ ተዘራው ዘር መሆኑን ለመረዳት አያዳ ግትም ። ምክንያቱም በመልካሙ መሬ ት ላይ ከወደቀው ዘር በስተቀር በሦስቱ ም የመሬት ዓይነቶች ላይ የተዘራው ሁሉ ቡቃያ ብቻ እንጂ አበባና ፍሬ እን ዳልታየበት በምሳሌው ለመረዳት ይቻ ላል ።


ስለሆነም እያንዳንዳችን የእግዚአብ ሔርን ቃል መስማት ብቻ ሳይሆን የሰ ማነው ሁሉ መልካም ፍሬ ያፈራ ዘንድ ከትንኰል ፤ ከቂምና ከበቀል እንዲሁም ከኃጢአት ሥራ ርቀን እውነተኛውን የጽድቅ መንገድ እየተከተልን በመም ህራን አማካይነት የሚነገረንን ቃለ እ ግዚአብሔር በልቡናችን ሥር እንዲሰ ድና ሥር እንዲይዝ ለመንግሥተ ሰማያ ትም የሚያበቃ ጥሩ የሆነ ፍሬ እንዲያ ፈራ ልቡናችንን በንስሐ አለስልሰን በ ምግባርና በሃይማኖት እንድናዳብረ ው ያስፈልጋል ።

ኢሳይያስ ወንድማገኘሁ

ወንጌል የሚሰጥበት አዳራሽ ለወደ ፊት በደንብ እስከሚሠራ ድረስ በማ ለት ያለውን ትንሹን አዳራሽ በማስ ፋት እንዲሠራና ያካባቢው ሕዝበ ክር ስቲያንም ሆነ አላፊ አግዳሚው በአጠ ቃላይ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማ ት የሚጓጉትን ክርስቲያኖች እንዲገለ ገሉበት አድርጓል ።

ታዲያ በአመት ውስጥ ይህን ያህል የሠራ ለሚቀጥለው አመት እንዴት ይሆን ? ከብዙ በጥቂቱ ከረጅሙ ባጭሩ የተሠራውን ሥራ ከዚህ ላይ ስንገታ የእለቱም ዓመታዊ በዓል በደብሩ ዋና አስተዳዳሪ በመምህር ኃይለ ኢየሱስ እጅጉ አማካይነት ፕሮግራሙ በጸሎት ተዘግቶ የበዓሉ ፍጻሜ ሆኖአል ።

ዲ/ ናሁ ሠናይ ቀለ
ደብረ መዊዕ



## ዓመታዊ በዓሉን.....

ከገጽ ፩ የዞረ

ልዩ ልዩ ዝግጅቶች ተደርገውበታል ።

እንግዲህ ከላይ እንደጠቀስነው አቶ አዳነ አንድሰውና መሰል የሥራ ባል ደረቦቻቸው እንዲሁም የዚህ ስብከተ ወንጌል የሥራ አመራር ኰሚቴዎች በአንድነት እጅና ጓንቲ በመሆን ለዚሁ ስብከተ ወንጌል መጠናከር ብዙ ጥረት አድርገዋል ወደፊትም ያደርጋሉ ።

ወደነበርንበት ነገር እንመለስና በመ ሠረቱ ይህ ስብከተ ወንጌል በዚህ ታላቅ ሥራ ላይ ሕዝብ ጧት ማታ በማሰባሰብ ላይ ቢሆንም ወንጌልን ከላይ እንደተጠ ቀሰው ያለው ሕዝበ ክርስቲያን ያላ

ወቀው እንዲያውቅ ያወቀው እንዲያሣ ውቅ በማሠብ ይህ ስብከተ ወንጌል ከተ ቋቋመ ጀምሮ ከቀን ወደቀን ፡ ከሣምንት ወደሣምንት ፡ ከወር ወደ ወር ብሎም ከአ መት ወደ ዓመት በመሸጋገር ላይ ስለሆነ ስሁላችን ደስ ሊለን ይገባል ። ምክንያ ቱም የልዑል እግዚአብሔርን ቃል የምን ሰማበትና የምናውቅበት እንዲሁም በቃሉ እምነን የምንጸድቅበት ነውና በመሆኑም የስብከተወንጌል የሥራ አስኪያጆች በዚሁ አላበቁም በሥራ አስ ኪያጅ ኰሚቴዎች አሣሣቢነት አስፈፃ ሚነት በሰበካ አስተዳደር አሳሳቢነትና ለሕዝቡ መሰብሰቢያ ይህ ስብከተ



www.ethiopianorthodox.org

# ልማት በቤተ ክርስቲያን ፡

በዛሬው ጽሑፋችን ለአንባብያን የምናቀርበው በአርሲ ሀ/ስብከት በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት አልፎ አልፎ ስለተቋቋሙትና ወደፊትም እንዲቋቋሙ ስለታቀዱት የልማት ተግባሮች ይሆናል ።

በዚሁ ሀ/ስብከት ስላለው የቤተ ክርስቲያን የልማት እንቅስቃሴ እንዲያስረዱን የሀ/ስብከቱን ሥራ አስኪያጅ ሊቀ ካህናት ታደሰ ካሣን ጠይቀናቸው የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥተውናል፡

፩/ በመንበረ ጵጵስናው አጠገብ የምትገኘው የደብረ ምጽላል ቅድስት ማርያም ሰበካ ጉባኤና ሀ/ስብከቱ በመተባበር በርከት ያለ ገንዘብ አውጥተው የቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር በእንጨት የነበረው በግንብ በመሠራት ላይ ይገኛል ፤ ቅጽሩ ይፈጃል ተብሎ የተገመተውም ብር ፶ሺ ስለሆነ የልማቱ አስተዋጽኦም በመቀጠል ላይ ነው ።

፪ አሰላ ደብረ ብሥራት ቅዱስ ገብርኤል ከጣሪውና ከግድግዳው በስተቀር የውስጥ ጽዳቱ አልተሟላም ነበር መብራትም አልነበረውም ከቅርብ ቀን ወዲህ ግን የልማት ኮሚቴ ተቋቁሞ ከምእመናን በተገኘው ፷ሺ ብር የጣውላ ምንጣፍና ኮርኒስ ተደርጐለታል ግድግዳውም ቀለም ተቀብቷል ከዚህም ሌላ ፬ሺ ብር የፈጀ መብራት ተጠልፎ ገብቷል ።

፫ በክፍለ ሀገሩ የሚገኙ የሕግ እሥረኞች የሚጸልዩበት ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራላቸው ስለጠየቁና የወሀኒ ቤቱም አዛዥ ድጋፍ በመስጠታቸው ፕላኑ ተዘጋጅቶ ቀርቦ አሠሪ ኮሚቴዎች ተመርጠዋል የሚሠራበትም ቦታ በብፁዕ አቡነ ናትናኤል ተባርኮ አሁን ሊጀመር በዝግጅት ላይ ነው ።

፬ በአሰላ ከተማ የሚገኘው የቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ቀደም ብሎ የተሠራ መሆኑ ቢታወቅም ከደረጃው በታች በሊሾ የተሠራው በዚሁ ደብር ከሚኖሩ ምእመናን ለልማት በተወጣጣው ገንዘብ ነው ፤ እስከ አሁን የጠቀስኩት በከተማው አካባቢ የሚደረገውን የልማት እንቅስቃሴ ነው ። ከከተማ ወጣ ብለን ስንመለከት ደግሞ ብዙ ልማቶችን እናገኛለን ።

ሀ/ በጭላሎ አውራጃ በኢጦሳ ወረዳ የምትገኘው የሂሩታ ማርያም ሰበካ



ሊቀ ካህናት ታደሰ ካሣ የአርሲ ሀ/ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ለቀረበላቸው ጥያቄ ማብራሪያ ሲሰጡ

ጉባኤ ሁሉም ያምርት በሚለው መሠረት ከገበሬ ማኅበር መሬት ጠይቆ በተሰጠው መሬት ላይ ሽንኩርት በመትከል ለቤተ ክርስቲያናችን ገቢ በማስገኘት ላይ ነው በዚህ ዓመት ብቻ የተሸጠው ሽንኩርት ፳ሺ፯፻፶ ብር ለቤተ ክርስቲያን ገቢ ሆኖአል ።

ይህም ከፍተኛ ገቢ እንዲገኝ የተባበሩት ብዙዎች መሆናቸው ባይካድም በይበልጥ ከፍተኛ ጥረት ያደረጉት በቦታው የሚኖሩት አባ አሥማረ አየለ ናቸው። ከዚህም ሌላ አንድ ግለሰብ በበጐ ፈቃዳቸው ቅጽረ ቤተ ክርስቲያኑን በሽቦ አሳጥረው ከሦስት መቶ ያላነሱ የወይራ አትክልትን ተክለው አጽድቀዋል ።

በተጨማሪም በዚህ ወረዳ የሚገኘው የበዓለ ወልድ ቤተ ክርስቲያኑንና ቅጽሩን አሠርቶ ያስረከበው አንድ ግለሰብ ነበር ፤ አሁን ቤተ ክርስቲያኑ እንደገና በመፍረሱ ሀ/ስብከቱ መንፈሳዊ ቅስቀሳ በማድረግ ፲ሺ.ህ ብር ከሕዝብ እንዲወጣ አድርጐ በጥሩ ሁኔታ እንዲሠራ አድርጓል ።

ለ/ በሙኒሳ ወረዳ ቀርሳ እግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራ ፕላኑ ወጥቶ ቀደም ሲል ከቫቲካን እምባሳደር የተጠየቀው የእርዳታ ገንዘብ ብር ፲፱ሺ.፰፻፵፯ ከ፹፫ ሳንቲም በልማት ኮሚሽን በኩል ለሀ/ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ናትናኤል ስለተላከ በዚሁ ገንዘብ የቤተ ክርስቲያኑ መሠረት ተጥሎ ከምእመናኑም አስተዋጽኦ እየተደረገ ሥራው በመጣደፍ ላይ ይገኛል ።

ሐ/ አርባ ጉጉ አውራጃ በጀጁ ወረዳ አዲስ ሕይወት ተብሎ ተሰይሞ ለድኩማን ማስፈሪያ በተሰጠው ቦታ ላይ ያሉት ድኩማኖች በወር ለእያንዳንዱ ፳ ብር የጡረታ አበል ከሚሰጣቸው በስተቀር ሌላ የሚረዱበት ገንዘብ አልነበራቸውም ፤ ከዚህም ሌላ እምልኮተ እግዚአብሔርን የሚገልጹበት ቤተ ክርስቲያን ስላልነበረ ከብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እርዳታ በመጠየቅ ለመጀመሪያ ፭፻ ብር ተፈቅዶላቸው በዚህ ገንዘብ መሠረቱን ጥለው ጉልበታቸውንና ገንዘባቸውን በማስተባበር ግምቱ ከ፳፭ሺ.ህ ብር በላይ የሚያወጣ ቤተ ክርስቲያን ሠርተው በብፁዕ አቡነ ናትናኤል ተባርኮ ታቦቱ ገብቶ በአገልግሎት ላይ ይገኛል ።

በተጨማሪም ወፍጮ እንዲተክሉላቸው ሀገረ ስብከቱን አሳስበው ሀገረ ስብከቱም ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አቅርቦ ከልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መመሪያ እንዲሰጣቸው በመፍቀዳቸው ወፍጮውን ተረክበው በሥራ ላይ አውለውታል ።

መ/ በዚሁ አካባቢ ተስፋ ሕይወት ማርያም የሚገኙት ድኩማኖች ቆፍረው ያመረቱት የሽንኩራ አገዳ ግምቱ ፲፭ሺ.ህ ብር ይሆናል በማለት የሀ/ስብከቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሊቀ ካህናት ታደሰ ካሣ በሀ/ስብከቱ በሚገኙ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት ስለሚያከናውኑት የልማት እንቅስቃሴ ገልጸውልናል ።



በሁለተኛው የሰበካ ጉባኤ ሥምረት ወደ አርሲ ሀ/ስብከት የተላኩት ልዑካን ብፁዕ አቡነ ናትናል በተገኙበት የትኡን አምዳል ይመለከታሉ

ለወደፊት ሊሠሩ የታቀዱ የልማት ተግባሮች እንዳሉ እንዲገልጹልን ጠይቀናቸው ሊቀ ካህናት ታደሰ ካሣ ሲገልጹ ፤

፩ኛ/ የሀገረ ስብከቱ የመሰብሰቢያ አዳራሽ ስለሌለው ስብሰባ በምናደርግበት ጊዜ እጅግ በጣም ስለሚቸግረን በቅርብ ቀን የመሰብሰቢያ አዳራሽ ለመሥራት አስበናል ።

፪ኛ/ በአሰላ ከተማ የሚገኙትን አምስት አብያተ ክርስቲያናት በማስተባበር አንድ የጉጆ ኢንዱስትሪ ለማቋቋም እቅድ አለን ።

፫ኛ በኮፈሌ ቅዱስ ገብርኤል አጥቢያ የሚኖሩ ካህናት የመኖሪያ ቤታቸው ከቤተ ክርስቲያኑ እጅግ በጣም የራቀ በመሆኑ በመውጣትና በመውረድ ብዙ ድካም ይደርስባቸዋል ይህንን ችግር ለማስወገድ ሀ/ስብከቱ ከአጥቢያው ሰበካ ጉባኤ ጋር በመመካከር አራት ክፍል ቤቶች ተሠርተው ካህናት ከዚያው እያደሩ እንዲያገለግሉ ለማድረግ ታስቦ አሁን ለመጀመር በዝግጅት ላይ ነው በተጨማሪም በዚሁ ደብር የዳቦ ቤት ፤ የሹራብ መሥሪያ ማሽን የከብትና የዶሮ እርባታ ለማቋቋም እቅድ አለን ሲሉ የሀ/ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ሊቀ ካህናት ታደሰ ካሣ ፡ ማብራሪያቸውን አጠቃለዋል ።

በአርሲ ሀ/ስብከት የተቋቋሙትን የልማት እንቅስቃሴዎች በጠቅላላ አልጠቀስናቸውም የጠቀስናቸው ከብዙዎቹ ጥቂቶቹን ነው ከልማት እንቅስቃሴዎች ጥቂቶቹን በጽሑፍ መዝግበን ለአንባብያን ያቀረብናቸው በአንዳንድ አህጉረ ስብከት የሚገኙ የሰበካ ጉባኤ አባላት ከልማት ተግባር እጃቸውን ሰብስበው ስለተቀመጡ ወደፊት በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የልማት ሥራዎችን እንዲያቋቁሙና ካህናትም በትርፍ ጊዜያቸው በልማት ተግባር እንዲሰለፉ ያደርጉ ዘንድ ለማሳሰብ ነው ።

ሐዋርያው ጳውሎስ "ምንት ብከ ዘኢነሣእከ እምካልዕከ" ከሌላው ያላገኘኸው ምን አለህ ብሎ እንደተናገረው አንዱ ሀ/ስብከት ከሌላው የመማር ፍላጐት ሊኖረው ይገባል ይህም ማለት የልማት ተግባር ያልጀመሩ አህጉረ ስብከት ከጀመሩት አህጉረ ስብከት ተምረው የልማት ተግባር የመጀመር ግዴታ አለባቸው ።

ስለዚህ የእያንዳንዱ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ካህናት እየቀደሱና እየጸለዩ በትርፍ ጊዜያቸው ፤ ኑሮአቸው የሚሻሻልበትን ቤተ ክርስቲያን የምታድግበትን የልማት ተግባር የማቋቋም ኃላፊነት አለበት ።

ካህናትም የሰበካ ጉባኤው አጥንቶ በሚመድባቸው የልማት ተግባር ጠንክር የመሥራት ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ሊያውቁትና ሊረዱት ይገባል ይህ የሆነ እንደሆነ ኑሮአቸውን ለማሻሻል ቤተ ክርስቲያንንም ለማበልጸግ የሚችሉበት ዘመን ሩቅ አይሆንም ።

ቄ. ልሣነ ወርቅ በዛብህ



www.ethiopianorthodox.org

# የመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን

የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የተ ባለች በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ት እዛዝና ፈቃድ በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ስም በፊልጵስዩስ አ ገር በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ሐዋርያት ያነጹትና የሕንጻው ሥራም በ፳ ቀን ተፈጽሞ በ፳፩ ቀን ፷፪ ዓ.ም. ቅዳሴ ቤቷ የተከበረው ታሪካዊቷ ቅድስት ቤተ ቤተ ክርስቲያን ናት ።


ይህንንም በ፳ ቀን የሚያበበው መጽሐፈ ስንክሳር የሚያስረዳ ሲሆን ታ ሪኩ በመጠኑ እንደሚከተለው ነው ይ ኸውም ሐዋርያት ጌታ ወደ ዓለም ሁሉ ሂዳችሁ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ አ ስተምሩ ባለው መሠረት ሁሉት ሁለት በመሆን በየሀገሩ እየተዘዋወሩ ወንጌልን በሚያስተምሩበት ጊዜ ቅ/ጳ ውሎስና በርናባስ እያስተማሩ ፊልጵስ ዩስ ከምትባል ሀገር ደረሱ ።

በዚያም ሕዝቡን አስተምረው አሳም ነው ከአሪት ወደ ሕገ ወንጌል ከአምል ኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔ ር መልሰው አጥምቀው በክርስቶስ ክር ስቲያን ካሰኟቸው በኋላ ትምህርት ለማ ዳረስ ወደሌላው አገር ወጥተው በሚሄ ዱበት ጊዜ የፊልጵስዩስ ሰዎች ተሰብስ በው አንድ ሁነን በክርስቶስ ካመንን ንድ ከእንግዲህ ወዲህ ባንድነት የምን ጸልይበትና የምንቀርብበት ቤተ ክርስ ቲያን ሥሩልን ሲሉ ቃቸው እንርሱም ሁኔ ታውን ገልጸው ወደ ኢየሩሳሌም ወደ እንትናዱስ ጴጥሮስና ዮሐንስ ላኩ ።

ቅዱስ ጴጥሮስና ዮሐንስም መልሰው እኛስ ያለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፈ ቃድ ምንም እናደርግም ነገር ግን እነር ሱ ለአንድ ሱባዔ ያህል እየጾሙና እየጸ ለዩ ወደ እግዚአብሔር እንዲያመለክቱ ንገሯቸው እንጅ አሏቸው ።

ወዲያው ሕዝቡ የሐዋርያትን ትእዛ ዝ ተቀብለው ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር ሱባዔ ገብተው በጾም በጸሎት ወደ እግዚአብሔር አመለከቱ ሱባዔው ከተ ፈጸመ በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን ከየሀገረ ስብከታቸው በደ መና አምጥቶ ቅ/ጳውሎስና በርናባስ ካ ሉበት ፊልጵስዩስ ሰበሰባቸው ።

ከዚህም በኋላ ቦታውን ለክተ ሰጥቷ ቸው ሥራውን ጀመሩ ወዲያውም ድን ጊያውን በተአምራት እንደ ሰም እያለ መለመላቸው መቅደስ ፣ ቅድስትና ቅኔ ማህሌት አድርገው በሕብረት ሠርተዋ ታል ። ይኸውም በሥላሴ አንድነት ሦ



የመጀመሪያይቱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በምድረ ጅቡቲ



ስትነት ምሳሌ ነው ቅድሩና ዙሪያው አ ንድ መሆኑ የአንድነታቸው ክፍሉ ሦ ስት ወገን መሆኑ የሦስትነታቸው ምሳ ሌ መሆኑን ያስገነዝባል ።

አንድ የቤተ ክርስቲያን ደራሲ አባ ጽጌ ድንግል ይህንን በማስመልከት ሲ ናገር በሠላስ አዕባን ገጸ ሥላሴሁ ለአ ምር ሐነፀ ቤትኪ ድንግል ድኅረ ፈጸመ ግርር ..... ብሏል ማኅሌተ ጽጌ ።

በዚህ መሠረት ከላይ እንደተገለጸው ሰኔ ፳ ቀን ሕንጻዋ ተፈጽሞ ፳፩ ቀን ጌ ታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለክብሯ እ ርሱ ሠራኢ ቄስ ሆኖ ቅዱስ ጴጥሮስ ሊቀ ሐዋርያት ተራዳኢ ቄስ ቅዱስ እ ስጢፋኖስ ሠራኢ ዲያቆን የቀሩት ሐዋ ያት በየመዓርጋቸው ሆነው ቀድሰዋል።

ነቢዩ ዳዊት አስቀድሞ በመንፈስ ት ንቢት ተገልጾለት ቀደሰ ማኅደረ ልዑል እግዚአብሔር ማደሪያውን ቀደሰ እርሱም በመካከሏ ስለሆነ ለዘለዓለ ም አትናወጥም መዝ.፵፭ ቁ.፬ ሲል የ ተናገረውን በዚህ መፈጸሙን ያመለክ ታል ቅዱስ ያሬድም ተቀድሰ መቅደስ ኃያል አቤተ እግዚአብሔር ለዛቲ ቤት ግሬራ አብ ቀዲሙ ለዛቲ ቤት ሐነፃ ወልድ ለዛቲ ቤት ወፈጸማ መንፈስ ቅ ዱስ በማለት የዘመረውም በዚህ መሠ ረት ነው ።

ሆኖም ሁሉንም በዚህ በርዝር ለመጥ ቀስ ስለሚበዛ በዚህ ገታነው እንጅ ይህ ብቻ አይደለም ይህን የመሰለ በየቦታው ይገኛል ።

በዚህም ወቅት ጌታችን ኢየሱስ ክር ስቶስ ራሱ በባሕርዩ ሥልጣኑ ያከበራት ና የቀደሳት ቤተ ክርስቲያኑ ያለጠባ ቂ መኖር የሌለባት መሆኑን ሲያስረዳ የቅዳሴ ቤቷን ሥርዓት ከፈጸመ በኋላ ቅዱስ ጴጥሮስን ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት አ ለቃ አድርጎ ሾሞቷል ።

በዚህ መሠረት ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሐዋርያት በየሄዱበት አህጉረ ስብከታ ቸው ሁሉ በእመቤታችን ቅድስት ድን ግል ማርያም ስም ቤተ ክርስቲያን መ ሥራት ስለጀመሩ ሥርዓቱ በየቦታው እየተስፋፋና እያደገ መጥቶ ዛሬ በየክፍ ላተ ዓለሙ ሁሉ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ አ ብያተ ክርስቲያናት ተሠርተው ተቋቁ መው ተደራጅተው ይገኛሉ ።

በአገራችንም በኢትዮጵያ ኦርቶ ዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እንኳን በአሁኑ ጊዜ ቁጥራቸው ከ20ሺ በላይ የደረሰ አብያተ ክርስቲያናት ተሠርተ ውና ተደራጅተው የሚገኙ መሆናቸው የታወቀ ነው ።

እንግዲህ በርዕሱ የተጠቀሰው የመ ጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ በ መጠኑ ተመልክተናል ። ይሁን እንጅ ቤተ ክርስቲያን ማለት ምን ማለት ነው? ከላይ እንደተመለከትነው ሁሉ ቤተ ክ ርስቲያን የሚለው ስያሜ ቦታውና ሕን ጻው ብቻ አይደለም ። ሁለት ዓይነት ፍች አለው ።

አንደኛው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምነው የተጠመቁት ምዕመናን የሚ ጠሩበት ሲሆን ሁለተኛው ከታሪኩ እን ደተረዳነው በክርስቶስ መሠረትነት ማ ህበረ ክርስቲያን ባንድነት ተሰብስበው የሚጸልዩበትና የሚቆርቡበት በጠቅላላ አምልኮተ እግዚአብሔር የሚፈጸሙ በት ቦታ መሆኑን ያመለክታል ።

ስለሆነም ስያሜው ለቦታው በሚሰጥ በት ቤተ ክርስቲያን ማለት የክርስቲያ ን ቤት ማለት ሆኖ ለምዕመን ሲሰጥ ግን ቤተ ክርስቲያን እንደማለት የክርስቶስ ማደሪያ ማለት ነው ።

ቃሉን ተቀብለው በእርሱ ያመኑና በፍቅሩ ጸንተው የሚኖሩ ምእመናን የእ ርሱ ማደሪያዎች መሆናቸውን ሲያስረዳ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወ ንጌል "ዘአፈቀረ ዘአቀበ ቃልየ እን ወአ በየ ወመንፈስ ቅዱስ ንመጽእ ኀቤሁ ወንገብር ምዕራፈ" የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል ቃሌን የጠበቀም እ ኔም የባሕርይ አባቴ አብ የባሕርይ ሕ ይወቴ መንፈስ ቅዱስም ወደ እርሱ እን መጣለን ማደሪያም (መኖሪያም) እናደ ርገዋለን ብሏል ዮሐ.፲፬ ቁ.፳፫ ።

ስለዚህ በወልድ ውሉድ በክርስቶስ ክርስቲያን የተባልን ሁሉ እግዚአብሔ ር አምላክ እኛን ከመውደዱ የተነሣ በ ሞትና ተፈጥሮ በእርሱ አምሳል የፈጠረን ከመሆኑም በላይ በኃጢአት ምክንያት ጠላት ቢያሸንፈንም ተቀዳ ሚና ተከታይ የሌለው የሚወደው አ ንድያ ልጁን ልከ ሕይወቱን ሠውቶ በ ደሙ የታደገን ለኛ መሆኑን በመገንዘብ ዘበእንቲኣ ለቤተ ክርስቲያን ተጸፋዕ ከ በውስተ ዓውድ ከመ ተቀድሰ በደም ከ ክቡር በክቡር ደምህ ከፍዳና ከኃጢ አት ታነጻት ዘንድ ስለ እርሷ (ምዕመን) በዓደባባይ ፊትህን ተጸፋህ ማስት መከ ራ መስቀልን ተቀበልክ እያልን ቸር ነቱንና ፍቅሩን በማሰብ እናመሰግነዋ ለን ። ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች ቤተ ክ ርስቲያን ከፓትርያርክ ጀምሮ እስከ አ ጸዌ ኆኅት ያለው ብቻ ይመስላቸዋል አ ይደለም በአጠቃላይ የክርስቶስ አማኝ የሆኑ ሁሉ ነው እንጂ ።

ሐዋርያው ቅ/ጳውሎስ ክርስቶስን በመ ርዓዊ ቤተ ክርስቲያንን (ምዕመናን) በ መርዓት እየመሰለ በማነጻጸር ሲናገር ማንም የገዛ ሥጋውን የሚጠላ ከቶ የለ ምና ነገር ግን የአካሉ ብልቶች ስለሆንን ክርስቶስ ደግሞ ለቤተ ክርስቲያን እን ደሚያደርግላት ይመግበዋል ይንከባከበዋ ል ..... ብሏል ። ኤፌ.፭ ቁ.፳፱

ይህም ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን ም ን ያህል እንደሚወዳት ያስገነዝበናል ይ ኸውም ከመውደዱ የተነሣ የእርሱን አር አያ በመከተል እንደ እርሱ ሕይወታቸ ውን በማሠዋት የሚጠብቋትና የሚንከ ባከቧት እረኞች ጠባቂዎች ሾሞላታል

በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔር ን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድር ጎ በሾመበት በመንጋው ሁሉና ለራሳች ሁ ተጠንቀቁ ሲል ቅዱስ ጳውሎስ መስ ክሯል የሐዋ.፳ ቁ.፳፰ ።

የቤተ ክርስቲያን ጠቅላላ ዓላማዋና ተግባርዋ ሰዎች ሁሉ በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የሚጠቀሙ በትን ነገር ማሳሰብና ማስፈጸም ስለሆነ የሚጠቀሙበት አገልጋዮቿ ብቻ ሳይሆ ኑ አባሎቿ ሁሉ ናቸው ።

ስለዚህ ፫፻፲፰ ሊቃውንት ሐዋርያት በሰበሰቧት ባንዲት ቤተ ክርስቲያን እ ናምናለን እንዳሉት ሁሉ በክርስቶስ ፈ

ወደ ገጽ ፲፱ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# አንድ ሰኔ የገደለውን ዘጠኝ ሰኔ አያነሣውም

ይህ አባባል የአንዳንድ ሠነፎችን ቸልተኛነት የሚጠቁም እንጂ የሰኔ ወር ራሱ ነፍሰገዳይ ነው ። ማለት አይደለም ይኸውም “ለዋኝ ሰኔ በጋው መስከረም ክረምቱ ”እንዲሉ እንኳንስ የዘሩትና የተከሉት ፍሬና ያልዘሩትና ያልተከሉት ማኘኛውም ነገር በሚበቅልበት በዚህ በዋናው የክረምት መቃረቢያ ወርኀ ወቅቱ የሚፈቅደውን ዘር መዝራትና ተክል መትከል ሲገባ እጅን አጥፎ እግርን አንጥፎ በመቀመጥ የአዝመራን ወቅት በከንቱ ማሳለፍ ራስን ከመግደል የማያንስ ወንጀል ነው ። ለቤተሰብም ላይ የሞት ቅጣት እንደመፍረድ ያህል ያስቆጥራል ።

የዓለም መድኅን ክርስቶስ ወንጌልን ይሰብክ በነበረበት ጊዜ የሚናገረው ቃል ሁሉ ወቅቱን የሚጠብቅ ስለነበር ለገበሬዎች ሲያስተምር መሬትን በምዕመናን ልብ ቃሉን በዘር የወንጌል መምህራንን በገበሬ እየመሰለ እንደነበር ተጽፎአል ። (ማቴ ፲፫’፩-፲፯) ይህም በአንድ በኩል የሥራን ክቡርነት የሚያስተምር ነው ።

ከብዙ ሥነ ምግባራት አንዱ ሥራ ወዳድነት ነው ። ባለቅኔው መሬት ሁሉን ነገር ተሸክማ ስትኖር የሚከብዳት የለም ከሰነፍ ሰው በቀር ” ሲል እንደተናገረ በክርስቲያን ዓለም እንደተግባረፈትነት አስከፊ ነገር የለም ። ምክንያቱም ተግባረ ፈት ሰው ራሱንና ቤተሰቡን ብቻ ሳይሆን ለሌሎች ሸክም በመሆኑ ጐረቤቱንና ወዳጁን ዘመዱን ሁሉ እስከማስቸገር ይደርሳል ።

ዕድሜያቸውን በቅልውጥ እንጀራ ለመግፋት የወሠኑ አንዳንድ ሰነፎች ወርቅ የሚዘንምበትን የአዝመራ ወራት በቦዘኔነት እያሳለፉ ችግር አንቆ በሚይዛቸው ጊዜ በየድግሡ ቤትና በየለቅሶው ቤት እየተዘዋወሩ የሰው እጅ አይተው ከመኖር በቀር ሌላ አጋጣሚ ያለ አይመስላቸውም ። እንደነዚህ ያሉ ቦዘኔዎች (ተግባር ፈቶች) በሐዋርያው ጳውሎስ ዘመን በተሰሎንቄ ይኖሩ ስለነበር በወቅቱ ቤተ ክርስቲያንን ገጥሞዋት ከነበረው ችግር ሁሉ መካከል በተለይ በቅልውጥ ሰዎችን የማሠልቸት የይሉኝታ ቢስነት ጉዳይ እንደነበር ከዚህ የሚከተለው ጽሑፍ ያስረዳል ።

“ወንድሞች ሆይ ሥራ ፈት ከሆነውና ከኛ በተቀበላችሁት ትምህርት መሠረት ከማይኖር የስም ክርስቲያን ሁሉ እንድትለዩ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዝዛችኋለን ። ምክንያቱም የእኛን ምሳሌነት መከተል እንደሚገባችሁ እናንተ ራሳችሁ ታውቃላችሁ ። እኛም ከናንተ ጋር በነበርንበት ጊዜ ያለ ሥራ ቦዝነን አልተቀመጥንም ። የማንንም እንጀራ በብላሽ አልበላንም ይልቁንም ከናንተ በማንም ላይ ሸክም እንዳንሆንበት በማሰብ ሌሊትና ቀን በመድከምና በመጣር እንሠራ ነበር ይህንም ማድረጋችን እናንተ የእኛን ምሳሌነት (አርአያነት) እንድትከተሉ ብለን ነው ። ከናንተ ጋር በነበርንበት ጊዜ ሲሠራ የማይወድ አይብላ የሚል መመሪያ ሰጥተናችሁ ነበር ። ይህንም ያልንበት ምክንያት በመካከላችሁ አንዳንድ ተግባረ (ሥራ) ፈቶች መኖራቸውን በመስማታችን ነበር ። እንደነዚህም ያሉት ሰዎች በሥርዓት መኖርን እንዲለምዱና ሠርተውም እንዲበሉ በጌታችን በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዝዛቸዋለን ። (፪) ተሰሎንቄ ፫.፮-፲፫)

ታዲያ እነአይሸምቱና እነ አያርሴ ይህን ቃል ሲያነቡ ምን ይሰማቸው ይሆን በእውነት ሙሉ ጤንነት እያላቸው የአዝመራን ወቅት ጠብቀው ቢሰሩ እንኳንስ እራሳቸውን ሌላውን መርዳት ሲችሉ በላያቸው ላይ የድግሥ ዳስ እስኪፈርስና የመከራ ድንኳን ተነቅሎ እስኪጠቀለል የአንዳንድ ሰዎችን ቤት የሙጥኝ ብለው በቅልውጥ መኖርን የሚመርጡ ቢኖሩ ፍጹም እምነት ከጎደላቸው ሰነፎች ተነጥለው አይታዩም ።

ሰሎሞን በምሳሌው የሰነፎችን አስከፊነት አበክሮ ገልጧል ። እርሱም በሰፊው ካስተማረው ቃል ባጭሩ የሚከተለውን ጥቅስ እንመልከት ።

“አንተ ሰነፍ ወደ ገብረ ጉንዳን ተመልከት መንገዱዋንም አስተውለህ ጠቢብ ሁን የክረምት ምግብዋን በበጋ ታዘጋጃለች ። አንተ ሰነፍ ከዕንቅልፍህ መቼ ትነቃለህ ? እስከመቼስ ትተኛለህ” (ምሳ.፮.፮-፲ ።)

እንግዲህ ከዚህ አባባል እንደምንረዳው ሰውን ያህል ፍጡር ከስንፍና የተነሣ የአዝመራን ወራት በከንቱ እያሳለፈ በራሱና በቤተሰቡ ላይ ድህነትን በመጋበዝ ከገብረ ጉንዳን አንሶ ከመገኘቱ የበለጠ ምን አሳዛኝ ነገር ሊኖር ይችላል በተለይም ምድር ለእርሻ ምቹ ሆና ሣለ በተግባረ ፈትነት ባዶ የዳቦ ቅርጫት ተንተርሶ በመተኛት ተመጽዋችሆኖ ለመኖር መብቃት እጅግ አሳፋሪነው።

ውቢቱ አፍሪካ የዓለም ምድረ ገነት ልንገርሽ ወይ ቅኔ በሚያሳዝን ስስት እንደደጋን ጉብጧል የአውሮፓ ሕዝብ አንገት ድንግል መሬትሽን አሻግሮ ያየበት ።

የራስሽ ሕዝብ ግን ለምን ይሆን በውነት ስንፍና እግር ብረት እንዲያ የሆነበት ለረኃብ ለዕርዛት ተጋልጦ ለሐፍረት ተንተርሶ መኛት ባዶ የዳቦ ቅርጫት እኩል ስለሆነ ሙያህ ከሌላው ጋር አይበጅህምና መጋለጡ ሳሸሙር ኃያል ጉልበት አለህ ጠላት ለመገፍተር የልማቱም ዕድገት መድኅን ነው ለሀገር ተባብረህ ለመሥራት አሁን ተነሥ ጀምር ።

ቁ/መክብብ አጥናው

### የመጀመሪያዪቱ …

ከገጽ ፲፩ የዞረ

ቃድና ትእዛዝ በፊልጵስዩስ ሐዋርያት የሠሯት ቤተ ክርስቲያንና ዛሬም ያላችው በዚያን ጊዜ በክርስቶስ እምነው ጸንተው በቤተክርስቲያን ይጸልዩና ይቄርቡ የነበሩት ምዕመናንና ዛሬም ያለን ሁላችንም የክርስቶስ አካል ማህበር ቤተሰብ መሆናችንን አውቀን አንድነታችንን ጠብቀን በፍቅር መኖር ይገባናል ። ለዚህም እርሱ በቸርነቱ ይርዳን

መልአከ ምህረት ዓምደ ብርሃን



# ዜና ሊቃውንት

ከአሁን ቀደም ደጋግመን እንደገለጽነው በዚህ አምድ ታሪካቸውን እያሰፈርን ለአንባብያን የምናቀርባቸው ሊቃውንት የሞቱትን ብቻ አይደለም ። በሕይወተ ሥጋ ያሉትንም ሊቃውንት እናቀርባቸዋለን ።



መልአከ ፀሐይ ሠረቀ ብርሃን ወረታ እኒህ ናቸው

በማስተማርና በማስተዳደር ቤተ ክርስቲያንን ያገለገሉ ሊቃውንት ታሪካቸውን በሚገባ መዝግበው ቢልኩልን በዚህ ዓምድ ላይ አሳትመን ለአንባብያን የምናቀርብ መሆናችንን እንገልጻለን።

በዛሬው ጽሑፋችን የምናቀርበው ስለመልአከ ፀሐይ ሠረቀ ብርሃን ወረታ የሕይወት ታሪክ ተጽፎ የተላከልንን ነው ። መልአከ ፀሐይ ሠረቀ ብርሃን በ፲፰፻፹፯ ዓ.ም. ሚያዝያ ፲፱ ቀን ጋይንት አውራጃ አንስታ ጊዮርጊስ ተወለዱ ።

በተወለዱ በ፲ ዓመታቸው ከትምህርት ቤት ገብተው ትምህርት ጀመሩና በ፲፫ ዓመታቸው ዳዊት ደገሙ በአንድ ሺ ዘጠኝ መቶ ዓ.ም. ወደ ወሎ ክፍለ ሀገር ሄደው ደሴ ከተማ መሪ ጌታ ኪሩብ ከሚባሉ የድጓ መምህር አምስት ዓመታት በመማር ፀዋትወ ዜማን በሚገባ አጠንቅቀዋል።

ከዚያ በኋላ በዚሁ ክፍለ ሀገር መቂት ወደተባለው ወረዳ ሄደው አለቃ ውቤ ከሚባሉ የቅኔ መምህር ስድስት ዓመታት በመማር ቅኔ ከነአገባቡ በሚገባ ጠንቅቀው ተምረው በመምህርነት ተመርቀው ማስተማር ጀምረዋል ። በመቀጠልም ፤

በጐንደር ክፍለ ሀገር ጋይንት አውራጃ ስማዳ ወረዳ ቃጨና ኢየሱስ አራት ዓመታት ወገራ ጉራሬ ማርያም ሦስት ዓመታት አዘዞ ተክለ ሃይማኖት ሁለት ዓመታት ቅኔ በማስተማር ብዙ ደቀ መዛሙርትን አስተምረው ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አስረክበዋል ከዚያም በኋላ ጐንደር ከተማ በምትገኘው ደብረ ኃይል በዓታ ቅኔ እያስተማሩ ራሳቸው አቋቋም በመማር ሰባት ዓመታት ኑረዋል ።

ቀጥሎም በዚህችው ደብር ግብዝና ተሾመው አምስት ዓመታት አገልግለዋል። በ፲፱፻፳፫ ዓ.ም. ጣቁሳ መኮንታ ኢየሱስን አለቅነት ተሹመው ቅኔ እያስተማሩ ሁለት ዓመታት ሠርተዋል ። በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. ጐንደር ከተማ የልደታ ቤተ ክርስቲያንን ተሹመው አስተዳድረዋል ።

በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም. የጣሊያን ፋሺስት በተንኮልና በዕብሪት ተነሣሥቶ ሀገራችን ኢትዮጵያን በሙሉ ሲወር በጐንደር ከተማ የኢጣሊያን ቆንሲል የነበረው ወደዚያው ወደለመደከው ሀገር ሂድ ተብሎ ጐንደርን ተሹሞ መጣ በዚህ ጊዜ የመልአከ ፀሐይ ሠረቀ ብርሃንን አለቅነት ሽሮ ያስተዳድሯት የነበረውን ቤተ ክርስቲያን አልቅና ለሌላ ሰው ሰጠባቸው እርሳቸውንም ከጐንደር ከተማ እንዳይወጡ ወስኖ የቁም እስር በማድረግ አጋዛቸው ።

የቁም እሥር በመሆን ከ፲፱፻፳፰-፲፱፻፴፬ ዓ.ም. ከቆዩ በኋላ ወደ ምድረ ሱዳን ተሰደው በካርቱም ከተማ ከኢትዮጵያውያን ስደተኞች ጋር ስለሀገራቸው ኢትዮጵያ ነፃነት የሚፈለግባቸውን አስተዋጽኦ ሲከፍሉ ቆይተዋል ።

ሰንደቅ ዓላማችን ከወደቀበት ተነሥቶ ሲውለበለብ ከራስ ብሩ ጋር ከነበረው የጦር ሠራዊት ጋር አብረው ወደ ሀገራቸው ኢትዮጵያ ተመልሰዋል ።

ጐንደር የነበረው የጣሊያን ጦር ፈጽሞ ድል እስከሚሆን ድረስ ጦርነቱ በሚደረግበት ቦታ ሁሉ ከኢትዮጵያ ጦር ሠራዊት ጋር ሆነው ስንቅ በማመላለስ የደከመውን በማበረታታት ጀግናውን በማደፋፈር ከፍ ያለ ውለታ ለሀገራቸው ውለዋል ።

ጠላት ድል ሆኖ ሀገራችን ኢትዮጵያን ለቆ ከወጣ በኋላ በ፲፱፻፴፬ ዓ.ም. በጐንደር ከተማ ደብረ ኃይል በዓታን ተሹመው ፳ ዓመታት በሚገባ አስተዳድረዋል። ከ፲፱፻፵፫-፲፱፻፶፫ ዓ.ም. ደግሞ ከጐንደር ከተማ በስተሰሜን የምትገኘውን ደብረ ፀሐይ ቁስቋምን አለቅነት ተሹመው አስተዳድረዋል ።

ከዚያም በአለቅነት በቆዩባቸው ጊዜያት በድርቡሽ ወረራ ጊዜ ፈርሶ የነበረውን የደብረ ፀሐይ ቁስቋም ቤተ ክርስቲያን እንዲታደስ አድርገዋል ።

ይህንንና ይህን የመሳሰሉ መንፈሳውያን ሥራዎችን በመሥራት ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ሲያገለግሉ የኖሩት መልአከ ፀሐይ ሠረቀ ብርሃን አሁን የ፺ ዓመት ሽማግሌ በመሆናቸው ጉልበታቸው ደክሟል ፡ ዓይናቸው ፈዝዟል፤ የሚረዳቸው ልጅ የሚረዱበትም ገንዘብ እንደሌላቸው ከሕይወት ታሪካቸው ጋር ተመዝግቦ ተልኮልናል ።

መልአከ ፀሐይ ሠረቀ ብርሃን በላኩልን ጽሑፍ መጨረሻ ላይ በሕይወት ታሪኬ ላይ እንደተገለጸው የ፺ ዓመት ሽማግሌ ስለሆንኩኝ ወደ አዲስ አበባ ለመምጣት አልችልም ።

ነገር ግን የአድባራትና ገዳማት አስተዳዳሪዎች የነበሩት መብታቸው በሚገባ ተከብሮላቸው እንደ አገልግሎታቸው የጡረታ አበል እየተከፈላቸው ስለሆነ እኔም ለቤተ ክርስቲያን ያገለገልኩት ዘመን ተገምግሞ የጡረታ አበል እንዲፈቀድልኝ ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አሳስቡልኝ በማለት መ ፀ ሠረቀ ብርሃን ወረታ ጽሑፋቸውን አ



www.ethiopianorthodox.org

ጠቃለዋል ።

ማጠቃሊያ ከመጽሔቱ አዘጋጅ

መልአከ ፀሐይ ሠረቀ ብርሃን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ያገለገሉት በአንድ አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን በሁለት መንገዶች ነው ይኸውም ፩ኛ በማስተማር ሲሆን ፪ኛ በእልቅና ነው ። ከዚህም ሌላ በተጨማሪ በጠላት ጊዜ ከኢትዮጵያ አርበኞች ጋር በመሰለፍ ባላቸው ኃይል ጠላትን ተዋግተዋል ።

ይህንን ሁሉ አገልግሎት አበርክተው አሁን ያለምንም ረዳት ያለምንም መጠጊያ ከችግር ላይ ወድቀው እንደሚገኙ መልአከ ፀሐይ ገልጸዋል ። የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት አለኝታ የሆነው ቅዱስ ሲኖዶስ እንደዚህ ያለውን አሳሳቢ ጉዳይ በቸልታ ሊመለከተው አይገባም እንላለን ።

የመ[illegible]ውን ወዳጅህን በምን ከፈንከው በሻሽ ሁለተኛው እንዳይሸሽ እንደሚባለው ለብዙ ዘመናት ለረዥም ወራት ቤተ ክርስቲያንንና ሀገርን ያገለገሉ ሊቃውንት ጉልበታቸው ሲደነግዝ ዓይናቸው ሲፈዝ የሚረዱበት ዓመት ጉዳና [illegible] አሁን በሥራ ላይ የሚገኙ ሊቃውንት ብቻ ድልወት ያገኙ ማለት ግማሽ አካልን በልብስ ተጉናጽፎ ግማሹን ለብርድ እንደመዳረግ የሚቆጠር ሞኝነት ይመስለናል ።

በሥራ ላይ ያሉት ሊቃውንት ሞራላቸው ታድሶ ሥራቸውን በሚገባ ለማከናወን የሚችሉት ከእነርሱ ቀደም ሲል የነበሩት ምሁራን በዕርጅና ምክንያት ሥራቸውን መሥራት ሲያቋርጡ የሚረዱበት አመች መንገድ የተከፈተ እንደሆነ ነው ።

ስለዚህ የባለ ታሪኩ መልአከ ፀሐይ ሠረቀ ብርሃን መብት ተጠብቆ እንደ አገልግሎታቸውና እንደ ድካማቸው የጡረታ አበል ቢከፈላቸው ለቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት የማያቋርጥ የአለኝታ ምንጭ ይሆናል ብለን እንገምታለን ።

ቄስ ልዑነ ወርቅ በዛብህ

## ማረሚያ

በትንሣኤ መጽሔት ቁጥር ፹ ገጽ ፳ ላይ የባንክ ቁጥር ፶፱፳፩ ጅቡቲ ተብሎ የታተመው በስሕተት ስለሆነ ፦

፩ በጅቡቲ በሚገኘው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቁጥር ፮ ፶፱

፪ በአዲስ አበባ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ አራት ኪሎ ቁጥር አንድ ፩ሺህ ፱፻፶፩ መሆኑን ስንገልጽ ለዚሁ በጎ ተግባር ሁላችሁም ለስጦታ እጃችሁን እንደምትዘረጉልን ተስፋ እናደርጋለን ።



# ሁሉም በሕብረት ሣሉ

ሁሉም በሕብረት ሣሉ የተባሉ እነማን እንደሆኑ ለመግለጽ ቢአስፈልግ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሥጋ ለብሶ በዚህ ዓለም በተመላለሰ ጊዜ ለመቶ ሃያ ቤተሰቦች የወንጌልን ትምህርት እንደመሠረተ ይታረካል ። እነዚህም አሥራ ሁለቱ ሐዋርያትና ሰብአ ሁለቱ አርድእት ሰላሣ ስድስቱ ቅድስት አንስትም ይገኙበታል ። መቶ ሃያ ቤተሰብእ የተባሉትም እነዚህ ናቸው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማስተማር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣና ወደ ሰማይ እስከ አረገበት ቀን ድረስ ከእርሱ ጋር አብረው እንደኖሩ ይነገራል ። በአርባ ቀን ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ እናንተ ግን ከሰማይ ሰማያዊ ሀብትን ሰማያዊ ዕውቀትን ገንዘብ እስክታደርጉ ድረስ በኢየሩሳሌም ተቀመጡ ብሎ ትእዛዝ ሰጥቷቸው ዓረገ ሉቃ ፳፬ ፥ ቁ.፶፩ ።

ከዚህ በኋላ ጽርሐ ጽዮን ተብሎ በሚጠራው የማርቆስ እናት ቤት የጸሎት ቤት ስለነበረ ሁሉም በሕብረት ሆነው የማኅበር ጸሎት እየጸለዩ ሣሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባረገ ልክ በአሥር ቀን በተነሣ በሃምሣ ቀን ከወደ ሰማይ እንደ አውሎ ነፋስ ድምፅ ያለ ድምፅ ሲነጉድ ተሰምቷል ።

ይህም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ እንደ ሆነ ተአውቋል ። ያሉበትንም ቤት መላው በእሳት አምሳል ላንቃ ላንቃ ያለው እሳት ሆና ታይቷቸዋል ። በሁሉም መንፈስ ቅዱስ አድሮባቸው ኃይል የሚሆናቸውን ሀብትና ዕውቀት ገንዘብ አድርገዋል ። ቀደም ብሎ በነቢይ ኢዩኤል አምስት ሺህ ከአምስት መቶ ዘመን ሲፈጸም በሥጋዊና በደማዊ ሰው ሁሉ የባሕርይ ሕይወቴ መንፈስ ቅዱስን አሳድርበታለሁ ተብሎ ተነግሮ ነበርና ኢዩኤል ፪፥፳፰ ።

እንግዲህ ትንቢት ይፈጸም ዘንድ አስራ ሁለት ሐዋርያትና ሰብዐ ሁለቱ አርድዕት፣ሰላሣ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው ፍጹም ዕውቀት ተገልጾላቸው በአእምሮ እንደ ጉለመሱ ተገል ጿል ።

ከዚያ በፊት በአንድ ዕብራይስጥ ቋንቋ ብቻ ይናገሩ የነበረ ኋላ ግን በ፸፪ቋንቋ ለመናገር ችለዋል ። በዚያ አጋጣሚ ጊዜ በዓለ ሠዊትን ለማክበር ከየሀገሩ ተሰብስበው የነበሩ ሰዎች በሰብአ ሁለት ቋንቋ ሲናገሩ ሰምተው የእንክሮ ድንጋጤ ደንገጡና እጅግ ተገረሙ ።

እንግዲህ ከመንፈስ ቅዱስ የሚገኝ ዕውቀት ሁሉ ተከፍሎና ሕፀፅ የሌለበት እምላካዊ ሥጦታ እንደ መሆኑ መጠን ተመሣሣይ አይገኝለትም ። ሰዎች ከሰዎች ቋንቋን ለመማር ከአንዱ ሀገር ወደ ሌላው በሄዱ ጊዜ ብዙ ዘመን አሣልፈው ከአንድና ከሁለት ቋንቋ የበለጠ አይጠቀሙም ከሰው የሚማሩት ትምህርት ሁሉ ብዙ ድካም የሚጠይቅ መሆኑ አይዘነጋም እነሱ ግን አንድ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ማዕበል ስለወረደላቸው በዕውቀት ባሕር ዋኝተዋል የሰባ ሁለት ቋንቋ ባለቤት ሆነዋል ።

ከመንፈስ ቅዱስ ሥጦታ ያገኙት ትምህርት ይህ ብቻ አይደለም ሌላም አስደናቂ ትምህርት አግኝተዋል ። ቅዱሳን ሐዋርያት መንፈስ ቅዱሳን ከመቀበላቸው አስቀድሞ ፍርሐትና መሸበር ይጸናባቸው እንደነበር ታውቋል ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን በፈቃዱ ለሞት አሣልፎ በሚሠጥበት ሌሊት አይሁድ ተሰብስበው ሊይዙት በመጡ ጊዜ ሐዋርያት ፈርተውና ደንግጠው ጥለውት እንደሸሹ ተገልጿል ። ቅዱስ ጴጥሮስም ለጊዜው ቢገኝም ለቀረበለት ጥያቄ ከፍርሃት የተነሣ ክርስቶስን እንደማያውቀው መስክሯል ከሙታን ከተነሣ በኋላም አይሁድን ስለፈሩ በዝግ ቤት ሣሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመካከላቸው ተገኝቶ ሰላም ለዕናንተ ይሁን ባላቸውም ጊዜ እጅግ እየፈሩ ሕልተጽናኑም ነበር ።

መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ ከፍርሃትና ድንጋጤ ነፃ ሁነዋል ። ፍርሃት ፣ ድንጋጤ ጠፍቶላቸው ስለክርስቶስ ያለ ፍርሃት መስክረዋል ። ለሃይማኖት ሰ[illegible] አብነት ሁነዋል ። በአላውያን አደባባይ ቁመው ያለምንም ፍርሃት መከራ መስቀልን ለመቀበል ጨክነዋል ። ማንኛውም ፀዋትወ መከራ ሊያስፈራቸውና ሊያስደነግጣቸው አልቻለም ።

እንዲያውም አሕዛብ በአደባባይ ሲገርፏቸው ሲደበድቧቸው እንደተሾመና እንደተሸለመ ሰው ደስ እያላቸው ይወጡ እንደነበር ተጽፎአል ። ስለመከራ ፈንታ የሚቀበሉትን የመንግሥተ ሰማያትን ክብር በማሰብ ደስ ይላቸው ነበር ምክንያቱም ቀደም ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተስፋ መንግሥተ ሰማያትን አስረድቷቸዋልና ነው ። ምድራዊ ሹመት ሽልማት ቀረብን ብላችሁ ልቡናችሁ አይሸበርባችሁ በባሕርይ አባቴ በእኔም እመኑ እንጂ በአባቴ ቤት መንግሥተ ሰማያት ብዙ መዓርግ ሀብታት አሉና በማለት ሰማያዊ ክብርን እንደ አዘጋጀላቸው ነግሮአቸዋል ።

እንግዲህ ቅዱሳን ሐዋርያት የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ከተቀበሉ በኋላ ፍርሃትን ፣ ሽብርን ፣ ድንጋጤንና መጠራጠርን የመሣሠሉትን ሁሉ መሰናክሎች ድል ነሥተው ከፍጹምነት ደረጃ ደርሰው መከራ መስቀልን በመቀበል ክርስቶስን መስለውታል ።

በዚህ አንጻር እኛም እያንዳንዳችን በጥምቀት አማካኝነት መንፈስ ቅዱሳን ተቀብለን፡የክርስቶስ ሥጋና ደም ተቀብለን የቅዱሳን ሐዋርያትን አሠረ ትምህርት ተከትለን ፤ ያልተማሩትን አስተምረን ፣ ያላመኑትን እንድናሣምን መንፈስ ቅዱስ ልቡናችንን በዕውቀት ያድስልን ።

መምህር ኪዳነ ማርያም አየለ



www.ethiopianorthodox.org

# እንደ እባብ ብልህ እንደ ርግብ የዋህ

እግዚአብሔር የሰውን ልጅ በምድር እንዲኖር ሲፈጥረው ምድርና መላዋን አመቻችቶ ለእርሱ እንዲሆን በማበርከብ ነበር ነገር ግን ለእርሱ ተገዥ ከሆኑት እንስሳት መካከል በአንዱ በእባብ ተታሎ የአምላኩን ትዕዛዝ ተላልፎ ተረገመም ምድርና ምላዋም ከርሱ ውድቀት የተነሣ ተረገሙ በተጨማሪም እንስሳትና አራዊት ዛሬ የያዙትን ጠባይ ሊይዙ ችለዋል የእንስሳትና የአራዊትን ጠባይ በየወገናቸው ስንመለከት የማይለወጥ ያው ቋሚ ሆኖ እንመለከታለን አንበሳው የአንበሳን እንጂ የነብርን በጉ የበጉን እንጂ የፍየልን ጠባይ ሲይዝ እንመለከትም የሰው ልጅ ግን የራሱ የሆነ ቋሚ ጠባይ ከውድቀት ወዲህ ስለሌለው ብዙ ጊዜ ተለዋዋጭ እንደሆነ እንመለከታለን ስለሆነም ኑሮውን በምድር ላይ ሲጀምርና አሁን ከደረሰበት የሳይንሳና የቴክኑዎሎጂ ደረጃ የደረሰው ጠባይንም ሆነ ጥበብን ብዙ ጊዜ ከፍጥረታት በመቅሰም እንደሆነ እንመለከታለን የሰውን ተለዋዋጭ ጠባይና የእስሳትንና የአራዊትን ጠባይ ሳይንስና ቴክኒዎሎጂ የፈለሰፋቸውን መሳሪያዎችንና ስነ ፍጥረትን ረጋ ብለን በናነጻጽር ይህ ነገር ግልጽ ሆኖ ማግኘት ይቻላል ።

የሰው ልጅ ጠባይ ከእንሰሳትና ከአራዊት ጠባይ ያልተሻለ ከመሆኑ የተነሳ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሲመላለስና ለደቀ መዛሙርቱ መመሪያ ሲሰጥ ከርግብ የዋህነትን ከእባብ ብልህነትን እንዲቀስሙ አስተምሯቸዋል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከትንኝ አንስቶ እስከ ትላልቅ እንሰሳትና አራዊት ድረስ በብዙ ምሳሌነት ቢቀርቡም ለጊዜው ወደ ዓላማችን በመሄድ በዚህ ክፍል የተጠቀሱትን ብቻ እንመለከታለን ።

እባብ በመሠረቱ የእባብን ጠባይ (ሕይወት) ስንመለከት በተፈጥሮው ተንኮለኛና ተናዳፊ ከመሆኑ ሌላ እጅግ በጣም ሲበዛ ብልህና ጥበበኛ እንደሆነ እንመለከታለን የሰው ልጅ ጠላት የሆነው ዲያብሎስም አዳምንና ሔዋንን ሊጥል የቻለው በእባብ ብልህነት ተጠቅሞ መልክም አግኝቶ ዘመድ መስሎ በመጠጋትና በምኞት በማስጐምጀት ነው ።

እባብ የሰይጣን መጠጊያ በመሆኑና ይህን በማድረጉ ቢረገምና እግሩ ወደ ሆዱ እንዲገባ አፈርም እየበላ እንዲኖር ቢደረግም ጠላቱን ለመጉዳትና ራሱን ለማዳን በጣም ጥበበኛና አስተዋይ እንስሳ ነው ከዚህም የዘነሳ ለመንደፍ በፈለገበት ወቅት በልቡ ዙስቦ ዙረከዝን ይጐዳል የሰው ልጅም ራሱን ሲመታው ሲፈልግ እባቡም ራሱን ላለማስመታት ባለው ብልህነት ራሱን ያቀብራል ተወንጭፎ ይወረወራል ወይም ወደ መሬት ይገባል ።

በትርጓሜ ወንጌል እንደሚተረከው ውሃ ለመጠጣት ሲፈልግ አስቀድሞ መርዙን አውጥቶ ካስቀመጠ በኋላ ውሃውን ጠጥቶ እንደገና መርዙን በአፉ ይዞ ይሄዳል ይህንንም የሚያደርገው የሚጠጣው ውሃ መርዙን አስራጭቶ እንዳይገድለው ነው በጥፋት ውሃ ጊዜም ኖኅ ለዘር እንዲተርፍ ወደ መርከቡ ካስፈራቸው እንስሳት አንዱ ስለነበር ርግብ በአፉ እንደ ጐጂ ተጠቅማ እንቁላልዋን ጥላና ቀፍቅፋ ጫጩቶቿን ይዛ እስክትወጣ ድረስ አፉን ከፍቶ የጠበቃት ብልህ እንስሳ ነውና ሰምን እንቁላሉን ቢበላ ኖኅ አውጥቶ እንደሚጥለው ስለሚያውቅ ሕይወቱን ለማቆየት የተጠቀመበት ዘዴ ነው እሥራኤላውያንንም በሲና በርሃ እየተጓዙ በእግዚአብሔር ላይ ሲያጉረመርሙ ስኮናከናቸውን ነድፎ የጣላቸውና በመጨረሻም ሙሴ ምስሉን ሰቅሎ የተነደፉት ሁሉ የተሰቀለውን ምስል ተመልክተው እንዲድኑ የሆነበት እንስሳ ይኸው እባብ ነው ለሰው ልጅ ውድቀት ምክንያት ስለሆነ በመጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ጊዜ ስሙ ተጠቅሶ የምናገኘው ለሰይጣን ተሰጥቶ ነው ራእይ ፲፪-፯-፲ ዮሐንስ ወንጌላዊ በተጨማሪ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ በደል ተሸክሞ ለዓለም ደኅንነት ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ ይሰቀላል ብሎ ጽፏል ዮሐ. ፫፣፲፭ ።

የርግብ የዋህነት በሰማይ ከሚበሩት አእዋፍ መካከል የዋህ ናት የጥፋት ውሃ በመጉደሉ አይታ እንድትመለስ ኖኅ ቢልካት በታማኝነት መልእክቷን ለላካት ጌታዋ በቋንቋ መግለጽ ባትችልም እንኳ በአፏ የወይራ ቅጠል ይዛ የተመለሰች ወፍ ናት ዘፍ. ፰፡፮-፲፪ ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በፈለገ ዮርዳኖስ በእደ ዮሐንስ ሲጠመቅ አብ በደመና "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው" ብሎ ሲመሰክር መንፈስ ቅዱስም በራሱ ላይ ያረፈበት በርግብ አምሳል ነበር ማቴ. ፫፣፲፮፣፲፯ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ መግለጫ ሆነው እንደምሳሌ ከቀረቡት መካከል አንዷ ርግብ መሆኗ የታወቀ ነው ። የተጠቀሱትን ፍጥረታት ሁኔታ ከተገነዘብን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዴት አድርጐ በምሳሌነት እንደተጠቀመባቸው እንመለከታለን ።

ዲያብሎስ የዚህ ዓለም ገዥ ነው ተብሎ ስለተጻፈ ዮሐ. ፲፬፡፴ ፪ ቆሮ. ፬፡፫-፬ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በምድር ላይ ያስተማረው ከቅንነት የዋህነት ነው ማቴ. ፲፩ ፡ ፳፱ መልእክቶቹንና ሥራዎቹን ስንመለከት ለተንኮለኞች ተንኮላቸውን በማስተዋል ለጥበበኞች እንደ ጥበባቸው ለአዋቂዎች እንደ እውቀታቸው መልእክቱን ሲያስተላልፍ በተጨማሪም ሰይጣን የእባብን ሥጋ በመልበስ ለውድቀትና ለሞት የተጠቀመበትን መንገድ ለድኅነትና ለሕይወት ለትንሣኤም ሲጠቀም በት እናያለን ማር. ፲፪፣፲፰-፳፯ ማቴ. ፳፪፣፲፭-፳፪ ዘፍ. ፫፣፲፭-፳፩ የሰይጣንን ራስ ቀጥቅጧል የእዳ ደብዳቤያችንን ደምስሷል በሰይጣን መርዝ ተበክለው የሞቱትን ሁሉ አንስቷል ቆላ. ፪፣፲፫-፲፭ ዕብ. ፲፪፣፩-፫ በሌላ በኩል ም በመስቀል ላይ ሰቅለው እየዘበቱበት ሳለ ፍጹም ርኅሩኅና ቸር ከመሆኑ የተነሣ አባት ሆይ የሚሠሩትን አያውቁምና ይቅር በላቸው" ብሎ ስለ ጠላቶቹ ጸለየ ሉቃ. ፳፫፣፴፬ በዚህ ሁሉ የክርስቶስን ሥራ ስንመለከት ብልህና አስተዋይ የዋህ ጥበብም የሞላበት ሲሆን በመ/ቅዱስ ውስጥ ከቶ ባንድም ቦታ በሥራውና በመልእክቶቹ የአንድም ሰው ሕይወት እንዲጐዳና እንዲጠፋ ሲያደርግ አናንብም ።

ጌታ ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ወንጌልን አስይዞ በዓለም ሁሉ ዳርቻ እንደ በጐች በተናዳፊና በነጣቂ ተኩላዎች መካከል የሚልካቸው ስለነበረ በሚሰጠው መመሪያና ትምህርት ላይ እጅግ ጥበበኞችና አስተዋዮች እንዲሁም የዋሆች እንዲሆኑ ከእባብ ብልህነትን ከርግብ የዋህነትን እንዲይዙ ይመክራቸዋል በተጨማሪ ግን የሚሰብኩት እርሱን ስለነበር የርሱን አሰረ ፍኖት ተከትለው መስቀሉን ተሸክመው እንዲከተሉት በሚገባ ነገራቸው አስተማራቸውም በዚህ ሁሉ በጊዜው ከነበሩት ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ሕይወት አንድ ነገር እንኳ በምሳሌነት እንዲወስዱ አልመከራቸውም እንዲያውም "ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠበቁ" ብሎ ጭራሹን ሲያርቃቸው እንመለከታለን ማቴ. ፲፮፡፮።

ሐዋርያት የክርስቶስን ፈለግ በመከተል በጥበብና በማስተዋል በየአሕጉራቱ ወንጌልን (የመሥራቹን) ይዘው ተጓዙ እስከ መስቀል ሞት ድረስም ተከተሉት በዚህ ሁሉ የተሰጣቸውን መልእክት በታማኝነት አድርሰው በድል ጐዳና ወደላካቸው ተመልሰዋል ።

የተጻፈው ሁሉ ለኛ ተጻፈ ስለተባለ ይህ ሁሉ ለኛ እንደተጻፈ ልናስተውል ይገባናል የወንጌል ሥራ ለሰው ልጅ ሁሉ መዳረስ እንደሚገባው ብናምንም በየዋህነት በእረያዎች ፊት እንዲሁ የሚጣል አይደለም በጥበብና በማስተዋል ለሚያስፈልጋቸው ነው እንጂ በዚያም ሆነ በዚህ እንደገና የሐዋርያነትን ኃላፊነት ትንሽና ትልቅ ሳይል በስሙ ለተጠሩን ሁሉ ስለደረሰ በማስተዋል የጊዜውን መንፈስ በመረዳት ቃሉን ልናሰራጭ እስከ መስቀል ሞት ድረስ ለላከልን ታማኞች ልንሆን ይገባናል ።

ስለዚህ እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብ የዋሆች ሆኑ ተብሎ ስለ ተጻፈ ተንኮል የሌለበትን ልባምነትንና የዋህነትን ይዘን በተላከንበትና በደረስንበት ሁሉ ይህን የደኅንነት ወንጌል ልናሰራጭ ይገባናል ።

ገዳሙ ደምሣሽ





www.ethiopianorthodox.org

# ማንን ላግባ

ካለፈው የቀጠለ

ጓደኛን መምረጥ

ክፍል 6

ሰዎች ለሥራ ተግባሮቻቸውና ለአ
ጠቃላይ ድርጊታቸው ሁሉ ረዳት ያስፈ
ልጋቸዋል ጽኑና ታማኝ ረዳት ለማግ
ኘት ደግሞ አስቀድመው ምርጫቸውን
ማስተካከል አለባቸው እያንዳንዱ ግለ
ሰብ የትዳር ጓደኛን ስለመምረጥና
ቋሚ ረዳትን ስለማዘጋጀት የነፍስ ወከ
ፍ አስተሳሰብና አስተያየት ሊኖራቸው
ይችላል ። በስነ ጋብቻ በሙል ጠለቅ
ያለ ምርመራና ጥናት ያካሄዱ ታዋቂ
የስነ ልቦና ሊቅ አሜሪካዊው ዶክተር
ሄንሪ እንዲህ ይላሉ "ጋብቻ የኩንት
ራት ኑሮ አይደለም እዋጋቢና ጣፋጭ
ፍሬ የሚሰጥ የማሠሪያ እንቀፅ ነው ።
በመሆኑም መርፌና ክኒን ከማያድነው
የማህበራዊ ደዌ ለመዳንና ፍፁም ጤነ
ኛ ለመሆንም ምርጫንም የማስተባበር
ተግባር የሚደገፍና ይቀጥል የሚባል"
ነው ። ይሉና ዶክተር ሄንሪ በሴቶችና
በወንዶች ሚዛን ያነሣሉ ብለው የገመ
ቱአቸውን ነጥቦች እንደየዖታው በም
ድብ ከፋፍለው ያቀርባሉ ።

ሀ. ሴቶች የሚያቀርቧቸው የመመ
ዘኛ ነጥቦች ፩ኛ በቁንብረት ያለውና
እራሱን ማስተዳደር የሚችል ፪ኛ. ቁጥጥ
ርና ተዕዕኖ የማያበዛ ፫ኛ ቀለብላባና
አመንዝራ ያልሆነ ፬ኛ በባሕልና በዕም
ነት ከሚመርጣት ጋር ተመሣሣይነት
ያለው ፭ኛ በንጽሕናና በአለባበስ ማዕከ
ላዊ የሆነ ፡ እነዚህን ነጥቦች ከአብዛኛ
ዎቹ የካሊፎርኒያ ሴቶች ተወያይቶ የወ
ሰድኳቸው ናቸው ። ይላሉ ሊቁ ሄንሪ
ወደ ሴቶች ብቻ አላተኰሩም ። ወን
ዶች የሚያምኑባቸውን የምርጫ ነጥ
ቦችም ዘርዝረዋል ።

ለ. የወንዶች የምርጫ ነጥቦች ፩ኛ
አስደሳች ውበትና መልክ ያላት ፪ኛ
በባልትና ሙያ የሰለጠነች ፫ኛ ጥሩ ትህ
ትናና ትዕግሥት የሚታይባት ፬ኛ መል
ካም ርህራሄና ሰበአዊ ሥነ ምግባር
የምታዘወትር ፭ኛ በዘር መድሎና በብ
ሄረሰብ ዝቅተኝነት የማታምን የሚ
ሉት ናቸው ዶክተሩ ግን ግራና ቀኝ
ያቀረቧቸውን ነጥቦች አልተቀበሉትም
የሴቶችን ነጥቦች ስንመለከት ይላሉ ።
ሊቁ ሴቶች ትናትና ጥርጣሬ ስለሚያሸ
ንፋቸው በራሳቸው የመመዘኛ ነጥብ
የትዳር ጓደኛቸውን በጋብቻ የእግር
ብረት ማሰር ሲሉ ራሳቸው በተግባር
የማይገልፁትን የህግ ጫና ያሸክማሉ
ይህም በራስ አለመተማመንና የስነ ልቦና
ድክመትን ያሳይባቸዋል ። እኒህ ሊቅ
ወንዶችንም ሴቶቹ ውሻ ይጮሃል በሚ
ለው ተረት ይጀምራሉ ።

ወንዶች በምግብና በጣፋጭ ቃል
እንዲሁም በሴት ውበት መታለል የረ
ጅም ጊዜ ልምዳቸው በመሆኑ ስለሚስ
ቶቻቸው ውበትና የጓዳ ሙያ እንጂ
በውጭ ስለሚያከናውኑት የሥራ ድርሻ
ደንታ ቢሶች ይሆናሉ ።ይልቁንም ወንዶች
ሳያስታውሉ ሴት ትዕግስተኛ ፡ ትህትና
ያላት ፡ ሰብአዊ ርህራሄና መልካም ስነ
ምግባር ያስተካከለች እንድትሆንላቸው
በመመዘኛ ነጥባቸው ላይ ተመኝተዋል
እርግጥ ነው ይህ ነጥብ ትዕቢተኛ ወንዶ
ች እንደሚአምኑበት በሴቶች ላይ አም
ባገነንነትና የበላይነትን ለማሳየት ሳይ
ሆን እኔ እንደምአምንበት ዕምነት
ላለው ትዳርና ለተቀደሰ ኑሮ
ይሁን የሚባል ነው ። እንዲህ ከሆነ
ደግሞ ነጥቡ ሴቶችን ብቻ ሣይሆን ወን
ዶችንም የሚያጠቃልል መሆን አለ
በት ።

በኔ በኩል ግን ሁለቱ ተፈላላጊዎች
ምርጫቸውን በሚከተሉት ነጥቦች
ቢያስተካክሉ መልካም ይሆናል ። ፩ኛ
ህብረት ባለው ሥራ ልቦናዊ ሥምምነት
፪ኛ በተመሣሣይ ዕምነትናሁለንተናዊ
ርዕዮት ፫ኛ በጠባይና በባህርይ መግባ
ባት ፬ኛ በጋራ ያሉትን ደካማ ጐኖች
በማስወገድ ፭ኛ ግልፅ የሆነ ውይይት
በማድረግ ሃፍረትንና ችግርን መፍታት
፮ኛ መረዳዳትና መደጋገፍ ፯ኛ ኑሮን
ለመልመድ ዕቅድንና ፕሮግራምን ማዘ
ጋጀት እነዚህ በአብዛኛው በህብረተሰ
ብአችን አእምሮ ኑሮ ቢሰርፁ ጋብቻ
ከፈጠረው የጭቅጭቅና ከውዝግብ
መድረክ አለም ባረፈ ነበር ። ዶክተር
ሄንሪ ሃሳባቸውን ሲያጠቃልሉ ምርጫ
የእጮኝነትን መንገድ ጠራጊ ነው
እጮኛነት ደግሞ የጋብቻ መሠረት
ነው ። ጋብቻም የህልውና (የኑሮ) አዳ
ራሽ ነው ። ብለዋል ።

ሊቁ ሄንሪ በዚህ አነጋገራቸው የወ
ጣቶች አባት የሥራ ጋብቻ ካሆን የጋ
ብቻ ጉዳይ አስወጋጅ ዕውቅ ሃኪም የት
ዳር ባለቅኔ ወ.ዘ.ተ.ረፈ የሚሉትን
መልካም ዝናና ስምን አትርፎላቸዋል።

ምርጫን ማስተካከልና በትክክለኛ
መንገድ ተጉዘው የጋብቻ ሃሳባቸውን
ዕልባት ለመስጠት ለሚሹ ወጣቶች
ሁሉ የዶክተር ሄንሪ አነጋገር ብቁና ተፈ
ላጊ መስፈርት ነው ። ትዳር ወሳኝና
አስፈላጊነቱም አያጠያይቅም ካልን
ከማግባት በፊት እራስን ማነፅና ምር
ጫን ማስተካከልና ጥሩ ኑሮን ለማዋ
ቀር ችላ የሚባል አይሆንም ትዳር አሳ
ሳቢና አመራማሪ ነጥብ መሆኑን ደጋግ
መን እንዳወሳን ሁሉ ምርጫችን የሚ
ደነቅ ፈለግ እንዲሆንልንም ማውሳቱ
አግባብ አለው ።የነቶሎ ቶሎ ቤት ግድ
ግዳው ሰንበሌጥ ከሚለው ድክመት
ለመዳንም ምርጫችን ማስተካከል አለ
ብን ።

ስለምርጫ ጉዳይ ከተነሣ አንድ ነገር
ትዝ አለኝ አልማዝና ተዋበች የሚባሉ
ሁለት እህትማማቾች ጋብቻን አስመ
ልክቶ የተለያየ ምርጫ ነበራቸው አል
ማዝ ህይወቷን ለመንፈሳዊ አገልግሎት
የሰጠውን ወጣት እንድታገባና የካህን
ሚስት በመሆንም እየተደሰተች ዘወት
ር እግዚአብሔርን እያመሰገነች ከባለቤ
ቷ ጋር ስትዘምር ስትጸልይ መኖር እንደ
ምትፈልግ ምርጫዋን በምኞት ትገ
ልፅ ነበር ። አልማዝ ይህ ምርጫ ካልተ
ሣካላት ግን በድንግልና ለመኖር እንደ
ወሰነች በምኞት ትገልፅ ነበር ። እግዚ
አብሔርም ምኞቷን ሰምቶ የህሊና ጸሎ
ቷንም ተቀብሎ ምርጫዋንአከናወነላ
ትና የካህን ሚስት ሆነች ።

እህቷ ተዋበች ግን በሴትኛ አዳሪነት
ተሰማርታ እዐያፈውና አስነዋሪው
ተግባር ምንም ሳይመስላት ታላቅ ቡና



ቤት ከፍታ ፡ ብዙ ሃብት ሰብስባ መኪና
እንደሸሚዝ እየለዋወጠች ተደስታ
ለመኖር ትመኝ ነበር ። ይህንንም የተመ
ኘችበት መልክና ፡ ውበት ስለነበራት
ነው ። እግዚአብሔር ግን ሃሳቧ የተቀ
ደሰና የተባረከ ስላልነበር ምኞቷ አል
ተፈፀመላትም ። የተመኘችው ቀርቶ
በተራ ተቀጣሪነት ብዙ ቀን ከደከመች
በኋላ ታማሚ ሆነች ። ይህም ራሱ ምር
ጫን አለማወቅ ነው ።

ለምሳሌ ከላይ የጠቀስናት ተዋበች
ከውበቷ ማማር የተነሳ ብዙ መራጭ
መጥቶላት ነበር ። እርሷ ግን መራጭ ይወ
ድቃል ከምራጭ እንደተባለው ምርጫ
ውን አልተቀበለችውም ነበር ። በገዛ
እራሷ ምርጫዋን ስለአበላሸችው እድሏ
ም ተበላሽና ካልሆነ ቦታ ወድቃ ቀረች።

ምርጫን በአስከፊ መልኩ ብቻ ሳን
መለከተው በምርጫቸው የተጠቀሙና
ይበል የተባሉ የትዳር ጓደኞች እንዳ
ሉም መግለፅ እንወዳለን ። ለምሳሌ
ይስሐቅንና ርብቃን ብናወሳ የሁለቱ ጋብ
ቻ በምርጫ የተከናወነ ሆኖ እናገኘዋ
ለን አብርሃም ለልጁ ለይስሐቅ ጥሩ
ሚስት እንዲመርጥለትና እንዲያጭለት
አሽከሩን ላከው መልዕክተኛውም ሲጓ
ዝ ከዋለ በኋላ ደክሞት ከምንጩ ዳር
አረፈ ብዙ ልጃገረዶች ውሃ ሊቀዱ መጥ
ተው ነበር ። ከእነዚህም መካከል ሁኔ
ታዋን አይቶ ውሃ እንድታጠጣው
ርብቃን ጠየቃት እርሷም አጠጣችው
ግመሎቹንም አጠጣችለት ። ዕንግዳ
መሆኑንና ማደሪያ እንደሌለው አውቃ
ለዘመዶችዋ ነገረች ከቤትም እንዲአድር
ተጠራ እግሩንም አጠበችው ለግመሎ
ችም ገፈራ አቀረበችላቸው መል
ዕክተኛውም የርብቃን ሥራዋንና ቁም
ነገርዋን አይቶ ለይሣቅ ሚስት እንድት
ሆነው መረጠለት እጫት ወላጆችም
ፈቀዱለት ለእጅዋ የወርቅ አምባር ለአን
ገቷም ድሪ ለጆሮዋም ጉትቻ በጠቅላላ
የሚገባውን ማጫ ሰጥቶ ይዞአት ሄደ ።
ይሣቅና ርብቃም ተጋብተው ልጆች
ወልደው እስከ ሕይወታቸው መጨረሻ
ድረስ በሰላም እንደኖሩ ታላቁ መፅሐፍ
ይነግረናል ። አሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ
፳፬ ቁጥር ፴፭ - ፷፯ ከእነርሱ የተወለ
ደው ያዕቆብም ቢሆን ራሔልን ሊያገባ
የቻለው በብዙ ድካምና ምርጫ እንደ
ሆነ ለማንም የተሰወረ አይደለም ።

የሰው ልጅ ታላቅ ነው የሚባለው
በአይምሮው ሃሳቢነቱ ክፉንና ደጉን
ለይቶ ፡ የሚሻለውን መርጦ ሲጠቀም
በመቻሉ ለገጠመው ነገር ሁሉ በምር
ጫው መወሰን መቻሉ ነው ። በመሆ
ኑም ምርጫችን የተሳካና ውጤቱም ያ
ማረ እንዲሆን እግዚአብሔር በመፀሐፍ
ቅዱስ ደጋግሞ አስተምሮናል ። ሌላው
ን ትተን "እሳትና ውሃ ቀርቦላችኋል
እጃችሁን እነሆ ወደመረጣችሁት መ
ጫመር ትችላላችሁ ።" የሚለው አም
ላካዊ ቃል ምርጫችንን እንድንአስተካ
ክል እና በአለማችን እንድንጓዝ ያበረ
ታታናል ። በአጠቃላይ ለጋብቻ ስም
ረት ፡ ለማህበራዊ ኑሮ አንድነት ፡ ለፍ
ቅርና ለሰላም ምርጫ ቀዳሚነት ያለው
የህሊና ሚዛን ነው ። ምርጫ በቸልተኝ
ነት ልናልፈው የማይገባን የድርጊታ
ችን ሁሉ መርህና ወሳኝ ነው ።

ጥሩ ቤተሰብ ለማፍራትና ክቡር በሆ
ነ የጋብቻ ሥነ ምግባር ተዋዶና ተከ
ብሮ ለመኖር ምርጫን ማስተካከል
ያሻል ስለዚህም መዝሙረኛው ዳዊት
መርጦ የማግባትን ጠቃሚነት ሲገልፅ
"ምስጉን ነህ መልካምም ይሆንልሃል
ሚስትህ በቤትህ እልፍኝ ውስጥ እንደ
ሚያፈራ ወይን ናት ፡ ልጆችህ በማዕ
ድህ ዙሪያ እንደወይራ ቡቃያ ናቸው"
ሲል ከመልካም ጋብቻ የሚገኙትን
ቤተሰቦች ባርኳል ። መዝሙር ፻፳፯
ቁጥር ፪-፫ እንዲህ ያለውን መልካም
ቤተሰብ ለማግኘት የተስተካከለ ምር
ጫና ጥናት ወሳኝነት አለው ።

በሚቀጥለው ጽሑፌ የጋብቻ ቋ ም
ንድን ነው ? በሚል ርዕስ እፅፋለሁ ።

ቀለመ ወርቅ መአሾ



www.ethiopianorthodox.org

# የግብርና በረከት

ሰዎች ለኑሮአቸው የሚያስፈልጉአቸውን ነገሮች ከተለያዩ እንስሳት ዕጸዋት አዝርዕት ያገኛሉ ። እግዚአብሔር አምላክ ሰውን በግንባርህ ወዝ ሥርተህ ደክመህ ብላ ብሎ ከአዘዘበት ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጅ ለፍላጐቱ ማሙአያ ለኑሮው ማሻሻያ የሚሆኑትን ከእንስሳት ከዕፀዋትና ከአዝርዕት ምርጥ የሆኑትን መርጦ በማርባት በመትከል በመዝራት ይጠቀማል ። ንጹሕ ዘር ለማግኘት ንጹሕ አስገኝ ያስፈልጋል የተጣራና ሰፊ ምርት ለማምረት የተጣራ ዘር መዝራት ያሻል ።

ዘሩ ሳይበጠር ከነክርዳዱ ከእነቆሻሻው ዘርቶ ንፁሕ ስንዴ አመርታለሁ ማለት ከበለስ ኩርንችት ይለቀማልን የተባለው ምሳሌ ዓይነት ይሆናል ። በንጽሕና በእንክብካቤ ጥሩ መኖ በመቀለብ ካልተያዘ እንስሳም ያማረ የወፈረ የደለበ እንስሳ አገኛለሁ ማለት የሕልም እንጀራ ይሆናል ።

ዛሬ በሀገራችን እንደሌላው እንደሰለጠነው ዓለም ከእንስሳትም ሆነ ከአዝርዕት ምርጥ ዘር በመምረጥ በሣይንሳዊ መንገድ በማዳቀልና በማርባት ላይ የሚገኙ ብዙ የሙከራ ጣቢያዎች አሉ። ከእነዚህም ምርጥ ዝርያ ከሚባሉት እንስሳት ለምሳሌ ያህል ብንጠቅስ በሲዳሞ ክፍለ ሀገር የቦረና ከብት ዝርያ የአርሲ የሐረር በጐንደር ክፍለ ሀገር የሚገኘው የፎገራ ከብቶች ምርጥ ዝርያ ከሚባሉት የሚመደቡ ናቸው ።

በዛሬው ጽሑፋችን በግብርና ሚኒስቴር የማስታወቂያና የሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት በወር አንድ ጊዜ እየተዘጋጀ ከሚታተመው ዜና ግብርና ከተባለው መጽሔት ቁጥር ፪ ገጽ ፲ በአንደሳ የእርባታ ጣቢያ ፫፻፶ የፎገራ የከብት ዝርያዎች እርባታ የሚለውን ርዕስ በመውሰድ የተሰጠውን ማብራሪያ እና ቀርብላችኋለን ።

በጐጃም ክፍለ ሀገር በባሕር ዳር አውራጃ በባሕር ዳር ዙሪያ ወረዳ በ፲፱፻፶፯ ዓ.ም. በ፭፻ ፶፪ ዶሮችና በ፫ የፎገራ ዝርያ ወይፈኖች እርባታውን የጀመረው የአንደሳ የእንስሳት እርባታ ጣቢያ በአሁኑ ጊዜ ፫፻፶ የፎገራ ዝርያዎችን በዘመናዊ የእርባታ ዘዴ በመጠቀም በማርባት ላይ እንደሚገኝ የእርባታ ጣቢያው ኃላፊ ጓድ ታደሰ ሐብቱ ገልጸዋል ።

የጐጃም የጐንደርና የወሎ ክፍላተ ሀገራትን የእንስሳት ሀብት ልማት ለማስፋፋትና በወተትና በሥጋ ምርት ታዋቂ የሆኑትን ከአካባቢው የዓየር ጠባይ ጋር በቀላሉ ሊላመዱ የሚችሉትን ምርጥ የከብት ዝርያዎችን እያረባ ለገበሬው በተለይም ለአምራቾች የኅብረት ሥራ ማኅበር ቅድሚያ በመስጠት ለማሻሻል ታስቦ የተቋቋመው ይህ የእርባታ ጣቢያ ከ፲፱፻፸፪ ዓ.ም. ወዲህ ተጠናክሮ በከብት መኖ ሥርቶ ማሣያና በሰው ሠራሽ ማዳቀያ ዘዴ የተደገፈ አገልግሎት ያበረክታል ።

በአሁኑ ጊዜ በእርባታ ጣቢያው ፪፻፲፱ ላሞች ፰ የፎገራ ኮርማዎች ፪ ፈሪሽያን የውጭ አገር ኮርማዎች ፶፭ ከ፰ ዓመት በላይ የሆናቸው ጥጆች ከ፰.፲፱ ወራት ዕድሜ ያላቸው ፳፩ የፎገራ ምርጥ ጥጆች እንዲሁም ፵፭ ጊደሮች በጠቅላላው ፫፻፶ የፎገራ ዝርያዎች ይገኛሉ ።

የእርባታ ጣቢያው የአካባቢውን የእንስሳት እርባታ ዘመናዊና ሣይንሳዊ ፈር ለማስያዝ ከዚህም የሚገኘውን የእንስሳት ክፍለ ኢኮኖሚ ለማዳበር በሚደረገው ጥረት አኳያ የተሟላ አገልግሎት ለማበርከት የባለሙያዎች እጥረት እንዳለበት የጣቢያው ኃላፊ ገልጸዋል።

ኃላፊው በተጨማሪም ሲአስረዱ እርባታውን ለማስፋፋት ከዚህ ቀደም ከተከለለው ፲፰ ጋሻ መሬት ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋለው ፭ ጋሻ መሬት ብቻ እንደሆነ ጠቅሰው ይህም በአጥር ካለመከለሉ የተነሳ ለዘመናዊ የግጦሽ ዘዴና ለተለያዩ የእንስሳት መኖ ሙከራዎች መስፋፋት አመች ሁኔታዎች እንዳይፈጠሩ ምክንያት እንደሆነ ጠቁመዋል

እንግዲህ ምርጥ የእንስሳት ዘርን ለማርባትና ለማግኘት ለእንስሳት የጤና ምርመራና ሕክምና ያስፈልጋቸዋል ። በዚህም መሠረት በዚሁ መጽሔት በገጽ ፮ ላይ እንደተገለጸው በዚሁ በጐጃም ክፍለ ሀገር በባሕር ዳር አውራጃ በባሕር ዳር ከተማ የተቋቋመው የባሕር ዳር ቀጠና የእንስሳት ጤና ጥበቃ ላቦራቶሪ ከ፲፱፻፸፫-፸፭ ባሉት ሦስት ዓመታት ውስጥ ለ፩ሺ፪፻፳፩ እንስሳት የተለያዩ የደም የአንጐል የእበት ምርመራ በአጠቃላይ የውስጥና የውጭ ጥገኛ በሽታዎች ምርመራ ማካሄዱን የላቦራቶሪው ኃላፊ ጓድ ዶክተር ካሣ ባዩ ገልጸዋል ።

ላቦራቶሪው ለእንስሳት ክፍለ ኢኮኖሚ ዕድገት ጠንቅ የሆኑትን ልዩ ልዩ በሽታዎችን በመመርመር ለጐረቤት ክፍላተ ሀገሮች ማለትም ለጐጃም ለጐንደር ለወሎ ክፍለ ሀገሮች አገልግሎት እንዲያበረክት ታስቦ በግብርና ሚኒስቴር በ፲፱፻፸፪ ዓ.ም. ከተቋቋመ ጀምሮ ናሙናዎችን በመሰብሰብ ተገቢውን ምርመራ ከማካሄዱም በላይ የሕክምና አገልግሎትም ጭምር አበርክቷል በማለት የጤና ጥበቃው ኃላፊው ገልጸዋል ።

ስለዚህ ከላይ እንደተገለጸው እንስሳትን ለማርባት ይህ ሁሉ ያስፈልጋል እያንዳንዱም ገበሬ ከብት አርቢ እንደዚህ ባለው ሣይንሣዊ ዘዴ ለመጠቀም እንኳን ባይቻል ለእንስሳቱ በመከር ጊዜ ገለባውን ጭዱን ድርቆሹን ደፋጨነውን በአካባቢው በቀላሉ የሚአገኘውን በመጠቀም ለከብቶች ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል ለእንስሶች ጥንቃቄና እንክብካቤ ብናደርግላቸው ጥቅሙ ለእኛ እንጂ ለእንስሳቱ አለመሆኑን ማወቅ የማይችል አለ ብለን አናምንምና ከእንስሳት ብዙ ጥቅም ለማግኘት ከፍተኛ እንክብካቤ ማድረግ ያስፈልጋል ።

ፍሥሐ ባንቴ



# ተተኪ ያስፈልጋል

ለማንኛውም ነገር መሰሉ አካሉ የሆነ ተተኪ ያስፈልጋል በመጀመሪያው ፍጥረት ጊዜ "ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት" የሚለውን የተፈጥሮ ፀጋ የተቀበለ የሰው ልጅ ተተኪ ትውልድ ያስፈልገዋል ማለት ነው ። በጠቅላላው የሚንቀሳቀስ ፣ የሚረባና የሚባዛ ሁይወት ያለው ፍጥረት ሁሉ ተተኪ እንደሚያስፈልገው ቢታወቅም ብዙ ዘመን ተደክሞባቸውና ተለፍቶባቸው እንክብካቤም ተደርጐባቸው የተገኙ ታላላቅ ዛፎች የቤተ ክርስቲያን አፀዶች ምሑራን የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትግን እጅግ በጣም ተተኪ ያስፈልጋቸዋል።

ስለ ሊቃውንቱ ተተኪ አስፈላጊ መሆን ከመናገራችን በፊት በሀገራችን የዛፎች ችግር ደርሶ እንደነበርና ተተኪም አስፈላጊ ሆኖ እንደነበር መጀመሪያ ብናወሳ የሊቃውንትም ችግር እንዳለና ተተኪም እንደሚያስፈልግ ልናውቅ እንችላለን ለምሳሌ ያማሩና የተወደዱ እንጨቶች ቢኖሩም እንኳ በሥፍራቸው ተተኪ ከሌላቸው ዋጋ የላቸውም ይህም ሲባል ጥድና ፣ ወይራ ሁለገብ መሆናቸው ይታወቃል ይሁን እንጅ ብዙ እንክብካቤ ከመፈለጋቸው ሌላ ተኰትኩተው አድገው ትልቅ ዛፍ ለመሆን አያሌ ዘመን ይጨርሳሉ ። በጣም የሚያስደንቀው ደግሞ ከተቆረጡ በኋላ አለመተካታቸውና ፣ አለማቆጥቆጣቸው ብቻ ሣይሆን ወዲያው እየደረቁ መሔዳቸው ነው ።

ለምሳሌ ባሕር ዛፍን የወሰድን እንደሆን በጥንካሬውና በአገልግሎቱ ከወይራና ከጥድ ቢያንስ እንጂ አይበልጥም ሆኖም ተወዳጅነትን ያገኘው በቶሎ ስለሚደርስና ቢቆረጥም ሥሩ እንደገና ስለሚያቆጠቁጥ ነው ። ይህም በመሆኑ ቀደም ባለው ዘመን የነበሩት አባቶቻችን ለቤት መስሪያም ሆነ ለማገዶ የሚያመቻቸው ተተኪ ዛፍ ሥለአጡ ዛፎች የሞሉበትን ሥፍራ እየመረጡ አዳዲስ ከተሞችን ሲቆረቁሩ ነበር የኖሩት ዳግማዊ ምኒልክ ግን ይህ ነገር የማያዛልቅና አገሪቱን የሚጎዳ መስሎ ስለታያቸው ቢቆረጥም በፍጥነት የሚተካውን ባሕር ዛፍ አስመጡ ሕዝቡ ሁሉ እንዲለምደውና [illegible] እንዲተክለው አደረጉ የአዲስ አበባ ከተማም ወደ ሌላ መዛወሩ ቀረ በዚያን ጊዜ ዛፎች በብዛት ስለተተከሉ ተተኪ ያስፈልጋል የተባለው ቃል ትርጉም አግኝቶ ነበር ።

ነቢያትን አህለው ሐዋርያትን መስለው የኒቅያና ፣ የኤፌሶንን ሊቃውንት ሆነው የሚሠሩና የሚተኩ መምህራንን ቤተ ክርስቲያን መተካት ያስፈልጋታል ። መቼም ርግብን ከእባብ እንቁላል ማግኘት አይሞከርም እንደዚሁም ብሔራዊውን ሥነ ሥርዓትና ብሔራውያንን ሊቃውንት ከውጭ ማግኘት አይቻልም ስለዚህ በቤተ ክርስቲያን አድገው ሥነ ሥርዓትዋንና ባሕሏን ፣ ብሔራዊ ትምህርቷን የሚያውቁ ራሳቸውን የሚገዙ እንደሚገባቸው የሚሠሩ እንግዳ ተቀባዮች ለማስተማር የሚበቁ ገንዘብን የማይወዱ ልጆቻቸውን በጭምትነት እየመከሩ የራሳቸውን ቤት በመልካም የሚያስተዳድሩ ሊቃውንት ናቸው ሊተኩ የሚያስፈልጉት።

ነገር ግን ብሔራዊውን ትምህርት ሳያውቅ የውጭ አገር ትምህርት ብቻ የተማረ አንድ ሰው ባንዲት ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በመንፈሳዊ አስተዳደር ሃላፊ ሆኖ እንዲያስተዳድር ቢሾም ፣ ችግሯን ያውቅላታል ፣ ሊቃውንቷን ይንከባከብላታል ፣ ሥነ ሥርዓቷን ይጠብቅላታል ማለት የበግን ግልገል ቀበሮ እያጠባች ታሳድግ እንደማለት ይቆጠራል ። ይህንንም ከአለፈው ከአፍሪካ ታሪክ ለመማር ይቻላል ። ቅኝ ገዥዎች አፍሪካን ወረው በነበረበት ዘመን የህዝቡን ሃብትና ንብረት ጉልበቱንም ጭምር መበዝበዛቸው አልበቃ ብሎአቸው ባሕሉንም ቅርሱንም ወረሱት ። ለምሳሌ ባሕል የአንድ ሃገር ሕዝብ የታሪኩ ፣ ያለባበሱ ፣ ያመጣጡና ያነሳሱ የዕድገት ሚዛን መሆኑ ይታወቃል ። የአፍሪካ ሕዝብ ግን ይህን መሳይ ዕድል አላገኘም ። ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት አፍሪካዊውን ሥነ ጽሑፍ ባሕል ፣ ፊደል፣ዕምነትና መንፈሳዊ ነገር፣ የሚያውቁ ሣይሆኑ የውጭውን ትምህርት ብቻ የተማሩ ሊቃውንት ባስተዳዳሪነት ወደአፍሪካ ስለገቡ ትውልዱን ያለባሕል አስቀሩት አገራችን ኢትዮጵያ ግን ከቀድሞው ጀምሮ እስካሁን ድረስ መንፈሳውያን ሊቃውንት ስለነበሯት የስነ ጽሑፍ፣የቅርሳቅርስ ፣ የታሪክ ባለቤት ሆና ኖራለች ።

ከላይ እንደተናገርነው ወይራና ፣ ጥድ ትልቅ ዛፍ ለመሆን የብዙ ዘመን ዕድገትና እንክብካቤ እንደሚያስፈልጋቸው የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንትም ከሊቅነት ደረጃ ለመድረስ አያሌ ድካምና ብዙ ጥረት እንደሚያሻቸው ከዚህ ቢበልጥ እንጂ አያንስም በእንዲህ ያለ ድካም የተገኙትን ሊቃውንት ቤተ ክርስቲያን እንደተራ ዕቃ መመልከት የለባትም ያማሩ የተወደዱ የቅርስ ዕቃዎች ስለሆኑ መንከባከብና መቆጣጠር ይፈለግባታል ። ይህንንም ያልንበት ያለ ምክንያት አይደለም ። ባሁኑ ጊዜ ሊቃውንት እያነሱና እየተወደዱ በመሔድ ላይ ናቸው ።

ለዚህም ሦስት ምክንያት አለው ፩ኛ የአሁኑ ትውልድ ይህን ያገኘ ይህን ይበላል ፣ የሚል ዘመን የወለደው ዘመናዊ የትምህርት ምስክር ወረቀት ሥለተፈጠረ ነው ። ይኸውም አንድ ግለሰብ ውጭ አገር ሔዶ በዚሁ አገር በሚገኙት መንፈሳዊ ኰሌጆች ተምሮ የበረታ ዲግሪ ፣ አቅሙ ያነሰ ዲፕሎማና ምስክር ወረቀት ይዞ መጥቶ ደህና ደመወዝ ያገኛል ። በዚህ ምክንያት ብሔራዊውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት የተማረ 4 (አራቱን) ጉባኤዎች ቢያውቅና መምህርም ቢሆን ፀዋተወ ዜማዎችንም ቢያውቅ ፣ ተመርቆም ምስክር ወረቀት ቢኖረው የእነዚህ ሁሉ ደመወዛቸው አነሥተኛ ስለሚሆንና ይህንንም ቢሆን በብዙ ችግር እንጂ እንደልዩ ስለማያገኙ ፈላጊው እያነሰ በመሔዱ ነው ተተኪ ያነሰው ።

2ኛ/ እንጀራው እንዳያልቅ ለወጡም እዘኑለት የሚል የጥንት ዘይቤ አለ ። የሊቃውንት ችግር እንዳይኖርና ተተኪ



www.ethiopianorthodox.org

ም እንዲኖር ከተፈለገ ፣ ብሔራዊ ትምህርትም እንዳይወድቅ ከታዘነለት እንደውጭው ትምህርት ይህንን የተማረ ይህን ያህል ደመወዝ ያገኛል የሚል የዲግሪ ፣ የዲፕሎማ የሠርተፊኬት ወይም የምስክር ወረቀት በሊቃውንት ተጠንቶ በሲኖዶስ የተወሠነ የትምህርት ደረጃ ቢኖር ኑሮ ባሉት ሊቃውንት ተተኪ በኖረ ነበር ይህ ባለመኖሩ ትውልዱ ወደዚህ ሊያዘነብል አልቻለም ።

3ኛ ቀድሞ የነበሩት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ሙያቸው ምን ነበር የሚለውን እስቲ እንመልከት ።

### የፃዋትወ ዜማ መምህራን

ችሎታቸው ፣ የዜማቸው ቅርፅ ፣ ላሕያቸው ፣ ዝግጅታቸው ፣ አቀራረባቸው ሥልታቸው ዝዩአቸው እንቅስቃሴአቸው ፣ ይትበሀላቸው ። እነዚህን የመሳሰሉት ሙያዎቻቸው በህዝብ ዘንድ የተወደዱና ለቤተ ክርስቲያንዋ ቅርስ መሆን የሚገባቸው ናቸው ።

የቅኔ መምህራንም ቢሆኑ ሙያቸው ከፍተኛውን ሥፍራ ይዞ ኑሯል ። ይኸውም ችሎታቸው ምርምራቸውና አስተሳሰብአቸው ፣ የቅኔአቸው ውበትና የሰምና ወርቅ አሰካኩቸው የሃረግ አጠላለፍና የአንቀፆች አመዳደባቸው ፣ የቅኔ መንገዶችን መልክ መስጠታቸውና ዘ.ማዎቻቸውንም ለልዩ ልዩ አገልግሎት እንዲውሉ ማድረጋቸው አገባባቸውን ከነዕርባ ቅምሮቻቸው ፣ ይትባህላቸውንም ጭምር ጠንቅቀው ማወቃቸው በጠቅላላው ከላይ የተጠቀሱትን የቅኔሙያዎች ለራሳቸው አውቀው ሌላውንም በማስተማራቸው በህዝብ ዘንድ ተወዳጅነትን አትርፈው ኖረዋል ። ላሁንም ትውልድ አንዳንድ ትዝታቸውን ትተው አልፈዋል ።

የመጻሕፍት ተርጓሚ መምህራንም ሰፋ ያለውን ቦታ ይዘው ኖረዋል ። ምርምራቸው ማመስጠራቸው ፣ ማራቀቃቸው ፣ ንባብን ማስታረቃቸው ፣ ጥቅስን መጥቀሳቸው ምሳሌን መመሰላቸው ፣ ሐተታን ማተታቸው ፣ መጻሕፍትን ከመጻሕፍት ማቀናጀታቸው ለአስረጂነት ተረትን ጣልቃ በማስገባታቸው፣ የትርጓሜን ሥልትና ዝዩን ማወቃቸው ለትርጓሜው ምልክት መስጠታቸው ይህን የመሣሰለውን ታላቅ ሙያ ይዘው ሕዝቡንና ቤተ ክርስቲያኑን ሲያገለግሉ ኖረዋል ። እነዚህ ሁሉ ጥንታውያን ሊቃውንት ሙያቸውንና ዕውቀታቸውን ለተተኪው ትውልድ ሳያካፍሉና በመዝገብ ሣያሰፍሩት ፣ በድምፅ መቅረጫ መሣሪያ ሳያስቀርሁ በማለፋቸው ቤተ ክርስቲያንን የሊቃውንት ችግር እንዳጋጠማት ለማንም የተሰወረ አይደለም ። አሁንም ያሉት ሊቃውንት ከዚህ ዓለም በሞት ከመለየታቸው በፊት ታስቦበት ሙያቸውና ዕውቀታቸው በድምፅ መቅረጫ መሣሪያ እንዲቀረፅና በጽሑፍም እንዲመዘገብ ለሕይወታቸውም ተገቢ እንክብካቤ ቢደረግላቸው መልካም ነው ። ለሚተኩትም ሊቃውንት የትምህርቱ ደረጃ ቢሻሻል ጠቃሚ ነው እንላለን ። ባለቤቱ ያቃለለውን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም ተብሎአልና ።

አለቃ ነቢየ ልዑል ዮሐንስ

---

## የእርጉዝ ሴቶች .....

ከገጽ ፳፫ የዞረ

ጨርቆች እና የሚተኛበት ቦታ እና የመሳሰሉት ፣

- እናትየዋ ከወለደች በኋላ የሚያስፈልጋትን ምግብ ቀደም ብሎ ማዘጋጀት በአጠቃላይ እርጉዝ ሴት በእርግዝናዋ ወቅት የራሷን ጤንነት መከታተል የህፃኑንም የአቀማመጡን ሁኔታ ለመረዳት እና ጤንነቱንም ጭምር ለማወቅ በአቅራቢያዋም በሚገኘው ሙያተኞች ክሊኒክ እና ሆስፒታል በመሔድ ምርመራውን መከታተል አስፈላጊ ነው ።

ተማሪ ነርስ መንበረ ምህረቴ



# የጤና ዓምድ

# የእርጉዝ ሴቶች የጤና አጠባበቅ

ከአፌ የሚወጣ ቃሌ እንዲሁ ይሆናል የምሻውን ያደርጋል የላክሁትንም ይፈጽማል እንጂ ወደ እኔ በከንቱ አይመለስም ኢሳ. ፶፭ ፣ ፲፩

እርግዝና ማለት ዕንሱ በእናት ማኅፀን ውስጥ የተፈጠረው የሚካሄደው የእድገት ደረጃ በእርግዝና ነው አንዲት ሴት እርጉዝ ከሆነችበት ቀን ጀምሮ እስከ ምትወልድበት ቀን ድረስ ያለው ጊዜ የእርግዝና ጊዜ ይባላል ወላድ የሆነች ሴት ከአሥራ አምስት እስከ አርባ አመት ባለው ጊዜ ውስጥ ለማርገዝ ትችላለች ፡

አንዲት ወላድ ሴት በእርግዝና ወቅት ለራሷ ጤንነት እንክብካቤ ማድረግ ያስፈልጋታል ። ይኸውም በምግብ በኩል የተመጣጠኑ ምግቦችን መመገብ ለሚወለደው ልጅ ጤንነት አስፈላጊ ነው ። ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ ሕፃናት ለመሞትና ለበሽታ ለመጋለጥ የሚበቁት በተለይ በእናታቸው ሆድ ውስጥ ማለትም ከመወለዳቸው አስቀድሞ ከተወለዱም በኋላ በቂ ምግብ ባለማግኘታቸውና ከንፅህና ጉድለት ጭምር ነው እንዲሁም የተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች እንደ ኩፍኝ ትክ ትክ ተቅማጥና ለመሳሰሉት በሽታዎች ይጋለጣሉ ከዚህም የተነሣ ብዙ ህፃናት ህይወታቸውን እስከ ማጣት ይደርሳሉ።

እናቶችን የወሰድን እንደሆን የመውለጃ ጊዜያቸው ሲቃረብ በምጥ ላይ እያሉ በማዋለድ ሙያ በሰለጠኑ ሞያተኞች በሠፈር ውስጥም ሆነ ወደ ጤና ጣቢያ በመሔድ ባለመረዳታቸው ምክንያት ብዙ ሥቃይ ይደርስባቸዋል ለምሳሌ የእንግዴ ልጅ ከእናትየው ማህፀን ግድግዳ ሳይለያይ እና ሳይወጣ ከቆየ ብዙ ደም ስለሚፈስስ ህይወታቸው እስከ ማጣት ይደርሳሉ ማለት ነው ።

በምግብ በኩል ህፃናት ቢያንስ እስከ አራት ወራት ድረስ የእናታቸውን ጡት መጥባት ያስፈልጋቸዋል ከዚያ ጊዜ ጀምሮ በተጨማሪ እንቁላል ወተት ፍራፍሬ እንዲያገኙ ማድረግ አስፈላጊ ነው ።

እርጉዝ ሴቶች በእርግናቸው ጊዜ ብዙ የአካል ለውጦች ይታይባቸዋል ።

በአካል ላይ የሚታዩ ለውጦች

የወር አበባ መቅረት

በጡቶች ላይ የሚታዩ ለውጦች የጡቶች ጫፍ ዙሪያ መጥቆር

የጡት መጠንከር እና ማደግ በአይን ሊታዩ የሚችሉ ጐላ ጐላ ያለ የደም ሥሮች ጠዋት ጠዋት የማስታወክ ስሜትና የማቅለሽለሽ ይህ ሁኔታ አብዛኛውን ጊዜ ከ፩ እስከ አስራ ስምንት ባለው ጊዜ ውስጥ ነው ፶% ያህሉ እናቶች ላይ ይህ ሁኔታ የተለመደ ነው። ነገር ግን በጣም ከበዛ ወደ ሐኪም ዘንድ ሔዶ ማማከር አስፈላጊ ነው ።

- ቶሎ ቶሎ የመሽናት ፀባዩ ይህ ሁኔታ የሚታየው ከአሥራ ሁለት ሳምንታት በፊት ነው ።
- የቆዳ ለውጦች ይህ ደግሞ የሚሆነው በሆድ ላይ እና በእምብርት አካባቢ የሚታዩ ምልክቶች ናቸው ።
- የሆድ ድርቀት በእርግዝና ወቅት በጣም አስቸጋሪ ከሆኑ ነገሮች አንዱ ነው ስለዚህ ውሃ በብዛት መጠጣት እና አትክልትና ፍራፍሬ እንዲወስዱ መምከር ያስፈልጋል ።
- የደም ሥሮች መታወክ በእርግዝና ወራት በእግሮች ላይ የሚታዩ የደም ሥሮች አሉ እንዲሁም እግር ማበጥም ይታይባቸዋል ። በዚህ ጊዜ በሚቀመጡበት ጊዜ እግራቸውን ከፍ አድርጐ መቀመጥና እረፍት በሚያደርጉበት ጊዜ መተኛት እንዳለባቸው መምከር አስፈላጊ ነው ። በምግብም በኩል የሔድን እንደሆን እንደ ብርቱካን ጐመን የመሳሰሉትን እንዲበሉ መምከር ተገቢ ነው ።

### የህክምና እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ምልክቶች

ደም የሚመስል ወይም ከደም ጋር የተቀላቀለ ፈሳሽ ሲፈሳቸው ኃይለኛና የማያቋርጥ ራስ ምታት የአይን ብዥ ብዥ ማለት ራስ ማዞር የፊትና የእግር ማበጥ እና እንዲሁም ከእርግዝናው ጋር የማይመጣጠን የክብደት መጨመር ወይም መቀነስ ።

የፅንሱ ከስድስት ወር በኋላ ፈፅሞ አለመንቀሳቀስ የማቅለሽለሽና ሃይለኛ ማስታወክ ስሜት እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ከፍተኛ ጉዳት ላይ ስለሚጥሉ ይህ ሁኔታ እንደታየ ወዲያውኑ ወደ ጤና ጣቢያው በመሔድ አስፈላጊውን እርዳታ ማግኘት አስፈላጊ ነው ።

እርጉዝ ሴት በእርግዝናዋ ወቅት በተቻለ መጠን ከበሽተኞች መራቅ ያስፈልጋታል ። በተለይ በሽታው ተላላፊ ከሆነ በጣም መጠንቀቅ አስፈላጊ ነው ። የቲታነስ(መንጋጋ ቆልፍ) ከሚባለው በሽታ እንድትጠበቅና እንዲሁም ህፃናት ከተወለዱ በኋላ ከዚህ በሽታ እስከ ሦስት ወር ድረስ እንዲጠበቁ ከ፬ወር ጀምሮ ለሁለት ጊዜ ትወጋለች። የሚያስፈልጓት ነገሮች አሉ ።

እርጉዝ ሴት በእርግዝናዋ ወቅት በሐኪም ያልታዘዙ መድሐኒቶች ለምሳሌ የአበሻ ኮሶ መጠጣት አስፈላጊ ፍሬ እና የመሳሰሉትን መጠቀም አስፈላጊ ነው ።

ሌላው ደግሞ የመውለጃዋ ጊዜ በሚቀርብበት ወቅት ረጅም መንገድ መሔድ ከባድ ዕቃ ማንሣት እንደሌለባትና እረፍት እንደሚያስፈልጋት መንገር አስፈላጊ ነው ።

በዚህ ወቅት እርጉዝ ሴት ማዘጋጀት የሚያስፈልጋት ነገሮች አሉ ። እነርሱም

- ለህፃኑ መጠቅለያ የሚሆን ንጹህ

ወደ ገጽ ፳፪ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

# ዓመታዊ በዓሉን አከበረ

የጉለሌ ደብረ መዊዕ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ሰብከተ ወንጌል ዓመታዊ በዓሉን ሚያዝያ ፳፩ ቀን ፲፱፻፹፮ ዓ.ም. በደማቅ ሁኔታ አከበረ ።

በዚሁ በታላቁ ቤተ ክርስቲያን ለመላው ዓለም አስደናቂና አኩሪ በተለይም ለኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን መመኪያና ከፈጣሪያቸው ጋር መገናኛ በሆነው ከ፯ በቀበሌ ፴፩ ውስጥ በሚገኘው ጉለሌ ደመዋዕቅ/ሚካኤል ፄተ ክርስተያን ውስጥ ይህ ስብከተ ወንጌል የምሥራችና ደስታን አሣይቷል ። በተለይም በዕለቱ የተገኙት እንግዶች ፦ የደብሩ ዋና አስተዳዳሪ የመንፈሳውያን ተማሮች ወላጅ ኰሚቴና የስብከተ ወንጌል የሥራ አስኪያጅ ፤ የደብሩ መንፈሳውያን ተማሮች ፡ከየአድባራቱ ጥሪ የተደረገላቸው መንፈሳውያን ልጆችና ምእመናን በፕሮግራሙ ላይ በመገኘት ለበዓሉ ድምቀት የሰጡት ከመሆኑም በላይ በዓሉን በታላቅ ስነስርዓት አክብረዋል ።

በዚህ በዓል የደብሩ ወጣቶች ልዩ ልዩ ያሬዳዊ የሆኑ መዝሙሮችንና መንፈሣዊ ግጥሞችን የመሣሡሉትን በዓሉን የሚመለከት ዝግጅት በማቅረብ ለበዓሉ የበለጠ ድምቀት የሰጡት ሲሆን በአንፃሩም ለበዓሉ ተስማሚ የሆነ ቲያትር በማዘጋጀት ለዚሁ በዓል ከፍተኛ ድምቀትን ሰጥተውታል ። ይህ ስብከተ ወንጌል ከተቋቋመ እነሆ ገና አንድ ዓመት ቢሆነውም ቅሉ በአንድ ዓመት ውስጥ ብዙ መንፈሳዊ ሥራዎችንና ስብከተ ወንጌልን በሚመለከት ለአካባቢው ምእመናንም ሆነ ለተዋህዶ እምነታችን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክቷል ። ወደፊትም ስብከተ ወንጌል ለቤ/ ክርስቲያናችን እድገት ለክርስትና እምነታችን ታላቅ ተስፋና አኩሪ እንደሚሆን ከሁኔታውና ከአለው ይዘት እንዲሁም አላማ ተረድተናል ።

በመሆኑም በዚሁ በዓል ስነስርዓት እንደተረዳነው በመጀመሪያ በደብሩ አስተዳዳሪ በመምህር ኃይለ ኢየሱስ እጅጉ አማካይነት ፕሮግራሙ በጸሎት ከተከፈተ በኋላ የዚሁ የስብከተ ወንጌል የሥራ አመራር ኰሚቴ ም/ ሊቀ መንበር የሆኑት መምሬ ጥላሁን ደሁን የወላጅ ኰሚቴው እስከ አሁን ድረስ ያከናወነውን ሥራ በማስመልከት ንግግር አድርገዋል ። ከዚያም የደብሩ የሰንበት ት/ ቤት ተማሮች ም ሊቀ መንበር የሆነው ዲ/ ናሁ ሠናይ ዋለ ለሰንበት ት/ ቤቱም ሆነ ስብከተ ወንጌልን በሚመለከት ሰፋ ያለ ንግግር አድርጓል ። ከዚህም በኋላ ለዕለቱ የተቀነባበረው ማለትም በመንፈሣውያን ወጣቶች የተዘጋጀው ትያትር ታይቷል ። ይህም ለበዓሉ ከፍተኛ የሆነ ድምቀት የሰጠው ከመሆኑም በላይ የክብር እንግዶቹንም ሆነ የአካባቢውን ምእመናን አስደስቷል ። በመጨረሻም የደብሩ ዋና አስተዳዳሪ መምህር ኃይለ ኢየሱስ እጅጉ በዓሉን በሚመለከትና የታየውን መንፈሣዊ ድራማ በማስመልከት ሰፋ ያለ ትምህርት ሰጥተዋል ።

ስለሆነም ይህ ስብከተ ወንጌል በአለፈው አንድ ዓመት ውስጥ ያከናወነውን መንፈሣዊ ተልዕኮ ከብዙ በጥቂቱ ለመግለጽ እንወዳለን ይህ ስብከተ ወንጌል ከላይ እንደገለፅነው የራሱ የሆነ የሥራ አመራር ኰሚቴ ሲኖረው በውስጡም የሰንበት ት/ቤቱን ያቀፈና አስፈላጊ የሆነውን አስተዋጽኦም ሆነ ቁጥጥር እያደረገ ክርስቲያናዊ የሆነ መንፈሳዊ ተልእኮ ያከናውናል ወደፊትም ከዚህ በበለጠ ይቀጥላል ይህ የሥራ አመራር ኰሚቴ በመጀመሪያ ስብከተ ወንጌል ከመቋቋሙ በፊት በቂ ወንበር ባለመኖሩ ለሕንፃ አሠሪ ኰሚቴዎች በመግለጽና እርዳታ እንዲያደርጉለት ጠይቋል የሕንፃ አሠሪ ኰሚቴውም ለዚህ ለተቀደሰ አላማ ስለቸኘ ሳይል እያንዳንዳቸው ከ፷ - ፶ ብር ድረስ በመርዳት ወንበር ሠርተው ለስብከተ ወንጌል የሥራ አስኪያጆች ሲያስረክቡ ይህም ኰሚቴ የራሱን የወላጅ ኰሚቴዎችን በማስተባበርና እንደሌሎቻቸው በመርዳት በተጨማሪም ከመንፈሣዊያን ወጣቶች ገንዘብ ተጨማሪ አድርጎ በቂ ወንበር አሰርቶ ለማንኛውም መንፈሣዊ ነገር አገልግሎት እንዲሰጥ አበርክቶአል አሁን ይህ ወንበርም በማገልገል ላይ ይገኛል ። ከዚህ ላይ ሳንጠቅሰው የማናልፈው ነገር ቢኖር አንዳንዶቹ ኰሚቴዎችም "ገንዘብ ብቻ አይበቃንም የምንቀመጠው ከቤ/ ክርስቲያናችን ቢሆንም በተለየም ለስብከተ ወንጌል ቢሆን እኔም ሆንኩ ቤተሰቦቼ በጠቅላላው ምእመናን ቢቀመጥበት በሰማይ እግዚአብሔር መቀመጫችን በበለጠ ያዘጋጅልናል" በማለት የቤታቸውን ምርጥ ምርጥ ወንበር በስጦታ አበርክተዋል ።

ይህ የወንበር ችግር ከተቃለለ በኋላ ለሕንፃ አሠሪ ኰሚቴዎችና በአካባቢው ለሚገኙት ለመላው ሕዝበ ክርስቲያን ስብከተ ወንጌልን እንዴት እንደሚያቋቁሙ ለመወያየት ጥሪ አድርጎ በዚህ ዕለትም በተለይ እንደ ኰሚቴው በመሆንና እንዲያውም በይበልጥ ለዚህ ስብከተ ወንጌል ጥረትና መልካም ድጋፍ ሃሣብ ያላቸው ለቤ/ ክርስቲያን አንጋፋና እንደሐዋርያ ጳውሎስ በመሆን የሚያገለግሉት አቶ አዳነ አንድሰው ለዚህ መልካም አላማና ተግባር ከመሰሎች አባቶቻቸውና እናቶቻቸው ወንድሞቻቸውና እህቶቻቸው በአጠቃላይ በአካባቢው ከሚገኙት ሕዝበ ክርስቲያን ጋር በመሆን ሚያዝያ ፳፬ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ስለ ሕንፃው ጉዳይ ያላቸውን አጀንዳ በማቆየት የሕንፃ አሠሪ ኰሚቴውን በሙሉ ይዘው ወደ አዳራሽ ገብተው በዕለቱ በስብሰባ የተገኙትን ሕዝበ ክርስቲያን በመቀስቀስና በማስተባበር ስብከተ ወንጌልን ሊያቋቁሙልን ችለዋል ፤ ሌሎችም የሥራ ባልደረቦቻቸው ይህንን ታላቅ ሕንፃ ለመሥራትና ለማስፈጸም የተዘጋጁት የኰሚቴ አባላት እንደ አንድ ልብ መካሪ ፣ እንደ

ወደ ገጽ ፩ ዞሯል



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፡

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፡

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፤ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፤ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰብችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፡

የስልክ ቁ. 116616
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፡

www.ethiopianorthodox.org